**<u>ጠቃሚ ማሳሰቢያዎች፡-</u>**

1ኛ) **በዚህ የቆላስይስ መልዕክት ጥናት ከዓላማ እና ከመግቢያው በተጨማሪ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የመልክቱ ታሪካዊ አውድ እና የጥቅሶች ትንታኔ ተሰጥቶቷል። ጊዜያችንን በትክክል እንድንጠቀም የትንታኔውን (የማብራሪያውን) ክፍል በቤታችን አንብበን እና ተዘጋጅተን መምጣት ይኖርብናል። ለጥናቱ በምንገናኝበት ጊዜ የጥናቱን ዓላማ፣መግቢያ እና የዕለቱን የንባብ ክፍል ብቻ በማንበብ ወደ መወያያ ጥያቄዎች መሄድ እንደሚያስፈልግ በትህትና እናሳስባለን።**

**2ኛ) ከዚህ በኋላ በየሳምንቱ ለጥናቱ ስንሰበሰብ ወንጌል በህይወታችን እንዴት እንደነበረ ወይም እየሰራ እንደሆነ (ለሌሎች ስለ መመስከር እና ስላሸነፍነው የህይወት ትግል) አንድ ወይም ሁለት ወገኖች እንዲመሰክሩ በማድረግ አመስግነን እንቀጥላለን። ወንጌልን መመስከር የሁላችንም ኃላፊነት ነው! ይሁንም! (1ኛ ጴጥ 2:9,2ቆሮ 5:18)**

**3ኛ) እንዲሁም ለዚህ ክፍል ጥናት አዲሱን መደበኛ ትርጉም መግቢያ ማንበብ ጥሩ ተጨማሪ እውቀት ይሰጠናል።**

**ጌታ ይባርካችሁ!**

ከቤተ ክርስቲያንቷ የትምህርት ክፍል

# ጥናት አንድ
## አጠቃላይ የቆላስይስ የጥናቱ መግቢያ

በአንድ ወቅት "አንድ ሳይንቲስት በእንቁራሪት ላይ ምርምር አደረገ። መጀመሪያ ውኃ አፈላና እንቁራሪቷን እዚያው ውስጥ ጨመራት። ውኃው በነካት ጊዜ እንቁራሪቷ ትዘል ጀመር። የፈላው ውኃ ሲያቃጥላትም አልሞተችም። ሌላዋን እንቁራሪት ደግሞ በቀዝቃዛ ውኃ ውስጥ ጨመራት። የውኃውና የእንቁራሪቱ የሙቀት መጠን ተመጣጣኝ ስለነበር ይህችኛዋ እንቁራሪት ሳትዘል ዝም ብላ ተቀመጠች። ከዚያም ሳይንቲስቱ ቀዝቃዛውን ውኃ እዚያው ውስጥ ካለችው እንቁራሪት ጋር አነስተኛ ሙቀት ባለው ምድጃ ላይ ጣደ። ውኃው ቀስ በቀስ እየፈላ ሄደ። የሚገርመው እንቁራሪቷ ምንም ዓይነት የመንፈራገጥ ምልክት ሳታሳይ በውኃ ሙቀት ተጠብሳ እስክትሞት ድረስ ዝም አለች"[1] ይባላል።

እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ እንደ ጨውና ብርሃን እንድትኖር ተጠርታለች። ነገር ግን ሰይጣን ወደ ቤ/ክን ሀሰተኛ ትምህርትን አሾልኮ በማስገባት ከእውነተኛ የቃሉ ጤናማ ትምህርት ወደ ተለየ ወንጌል ዞር እንድትል እና የዓለም እሴቶችና የአኗኗር ስልቶችን ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በማስገባት በአማኞች ዕምነት እና አኗኗር ላይ በዘመናት ሁሉ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኗል።

በእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ በጥንቃቄ ካልታየ በስተቀር የሀሰት ትምህርቶች ወደ ቤ/ክ ሲገቡ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብዙ አታላይ ነገሮችን በመጨመር እና በመቀነስ ነው። የቆላስይስ መልዕክት ለእንደዚህ ዓይነቱ የሀሰት አስተምህሮ ጥሩ ማሳያ የሚሆን ትምህርት አለው። ለቤተ ክርስቲያን እጅግ አደገኛ ከሆኑት ነገሮች አንዱ **ዓለማዊነት** ነው። ዓለማዊነት ከሁለት ገጽታዎች የሚመጣ ነው። <u>**የመጀመሪያው፥ እምነትን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኝ ንጹሕ ወንጌል የማቀላቀል ዓለማዊነት ነው።**</u> <u>በዚህ ፋንታ የሐሰት አስተማሪዎች ሌላ ወንጌል ያቀርቡልናል። አንዳንዶች በክርስቶስ ከማመን ላይ ሰናይ ምግባራትን ይጨምራሉ። ሌሎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሌለ የተስፋ ቃል ይጨምራሉ</u>

[1] ከአዲስ ማብራሪያ የተወሰደ

(ለምሳሌ፥ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ሀብታም ያደርጋል የሚሉ የብልጽግና ሰባኪዎች።) ሌሎች ደግሞ የክርስቲያኖችን የሚመስል አምልኮ እያካሄዱ አንድ-በሦስት የሆነውን (የስላሴ ትምህርት ) እግዚአብሔርን ይክዳሉ (ለምሳሌ፥ «ኢየሱስ ብቻ» እና "የቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት/አገልጋዮች ከቃሉ የላቀ ሥልጣን)።

ይህ ሁሉ በእውነት ላይ የተመሠረተ አምልኮ የሚፈልገውን አምላክ ደስ እንዳናሰኝ ለማደናቀፍና እምነታችንን ለመለወጥ ሰይጣን የሚያደርገው ጥረት ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙም ሳይቆይ አባሎቻቸው ሐሰተኛ ትምህርቶችን እንደሚቀበሉ በመግለጽ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች አስጠንቅቋቸዋል (በሐዋ. 20:30)።

**ሁለተኛው ዓይነት ዓለማዊነት የሚመጣው ክርስቲያኖች የዓለማውያንን እሴቶች ተቀብለው እንደ ዓለማውያን ሲኖሩ ነው።** ዓለም ወሲባዊ ኃጢአትን ታደፋፍራለች። ብዙውን ጊዜ ይህ ችግር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይታያል። ዓለም ትምህርት፥ ሀብት፥ እንዲሁም ቁሳዊ ቅርስ ወሳኝ ነገሮች እንደሆኑ ታስተምራለች። ብዙ ምእመናንም ይህንኑ አስተሳሰብ ይጋራሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ የቆላስይስን ቤተ ክርስቲያን ጎብኝቶ አያውቅም ነበር። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ አንዳንድ ዓለማዊ ፍልስፍና ክህደቶችን እየተቀበለች መሆኗን በሰማ ጊዜ፥ ደብዳቤ ጻፈላት። ብዙውን ጊዜ መናፍስትን ለመለየትና (1ኛ ቆሮ. 12፡10) ዓለም የምታስተምራቸውን ፍልስፍናዎች በቤተ ክርስቲያን ላይ የሚያደርሱትን ጥፋት ለመመልከት ትልቅ ጥበብን ይጠይቃል። ብዙውን ጊዜ የሐሰት ትምህርትና ዓለማዊ አኗኗር ጥፋቶች ቀስ በቀስ ወደ ሕይወታችን ውስጥ ስለሚገባ ሳትንፈራገጥ ተጠብሳ እንደሞተችው እንቁራሪት አደጋውን ለይተን ለማወቅ እንቸገራለን። ሐዋርያው ጳውሎስ የሐሰት ትምህርት እሳት እየጎዳቸው እንደሆነና ወደ ጥፋትም እንደሚወስዳቸው ይነግራቸዋል። ጳውሎስ በክርስቶስ ወንድሞቹና እኅቶቹ የሆኑት ክርስቲያኖች በስሕተት ሕይወት እንዲመላለሱ

አልፈለገም። ጳውሎስ የሐሰት ትምህርቶች ሊጋለጡና ሐሰትን የሚከተሉ ሰዎች ግልጽ ውሳኔ ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ተረድቶ ነበር።

በዘመናችንም ጤናማ የሚመስሉ የሀሰት ትምህርቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ የሀሰት አስተማሪዎች እና መንገዶች ሾልከው እየገቡ መሆኑን ጥያቄ የለውም። የብልጽግና ወንጌል ክርስቶስ ካመንን ሀብታሞች እንደምንሆን ይናገራል። ሌሎች ደግሞ ብናምን ከሁሉም ዓይነት በሽታ እንደምንፈወስ ያስተምራሉ። እንደ ኢየሱስ ብቻ፥ የይሖዋ ምስክሮች፥ ሞርሞኖች፥ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴና የመሳሰሉት ሃይማኖቶች ክርስቲያኖች ነን የሚሉትን ሰዎች እያወኩ ናቸው። ለረዥም ጊዜያት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች ቤተ ክርስቲያናቶቻቸውን ለቅቀው በመሄዳቸው ሲማረሩ ቆይተዋል።

## ***<u>ይህ ጥናት በአሁን ወቅት ለምን አስፈለገ?</u>***

ስለዚህ የሰይጣን ውሸት በማጋለጥ በስሕተት ውስጥ የሚወድቁ ምዕመኖቻችንን ለማስጠንቀቅ ጊዜው አይደለምን? መሪዎች ዛሬ ለዚህ ችግር ምላሽ የሚሰጡበትን መንገድ ለማወቅ ጳውሎስ በቆላስይሳ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተፈጠረውን የሐሰት ትምህርት ከተከላከለበት ሁኔታ የምንቀስመው እውቀት ይኖራል::

፩. በአሁኑ ዘመን የቤ/ክርስቲያንን ትኩረት ከክርስቶስ ይልቅ ሌሎች ነገሮች ለማሳብ እየታገላት በመሆኑ በመልዕክቱ ዋና እና የበላይ የሆነውን ማሳየት
፪. በግላችን የክርስቶስን የበላይነት መንፈሳዊ እውቀት በማሳደግ ከተለያዩ ስህተቶች ራሳችንን እንድንጠብቅ አና ሌሎችንም እንድናግዝ

## **<u>የመልዕክቱ አወቃቀር (አራቱ ምዕራፎች)</u>**

፩. ክርስቶስ የሁሉ የበላይ ነው (ቆላ 1)
፪. የተለያዩ የሀሰት (የኑፋቄ) ትምህርቶች ትንተና እና ማስጠንቀቂያዎች (ቆላ 2)
፫. የክርስቶስን ከሁሉ የበላይነት ትምህርት በኑሮ መግለጥ (ቆላ 3:1-4:6)
፬. ማጠቃለያ (ቆላ 4፡7-18)

ብዙዎች የቃሉ አስተማሪዎች የሚስማሙበት የመልዕክቱ ቁልፍ ቃል ያለው **በቆላ 1:15** ላይ ይሆናል። በመልዕክቱ ብዙ ሰዎች የተጠቀሱ ቢሆንም ጢሞቴዎስ፣ ኤጳፍራ፣ቲኪቆስና አናስሞስ፣ሉቃስ፣ማርቆስ በዋናነት የሚታዩ አገልጋዮች ናቸው (ይህንን በጥናቱ ውስጥ እናገኛቸዋለን)።

**ዛሬ የሚከተሉትን ጥቂት ጥያቄዎችን መወያየት እና ለሚቀጥለው የቆላስይስ መልዕክት ጥናት መጸለይ ይሆናል።**

1. **ከላይ ባነበብነው መሠረት በእቁራሪቷ ላይ በተደረገው ቤተ ሙከራ ምን እንማራለን?**
2. **ሰይጣን ቀስ በቀስ የሐሰት ትምህርቶችንና ዓለማዊነትን በማምጣት ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት ሲሞክር ያያችሁበት ሁኔታ ካለ ተወያዩ።**
3. **የመጀመሪያው አለማዊነት ትምህርት ምን ምንን ያጠቃልላል? ተወያዩ? በአሁን ዘመን እንዲህ ዓይነት ትምህርቶች ካሉ ጥቀሱ?**
4. **የሐዋ. 20፡28-31 አንብብ። ጳውሎስ የኤፌሶንን ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያስጠነቀቀው ስለ ምንድን ነው?**
5. **የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለዚህ ዓይነቱ ችግሮች ምን ዓይነት ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል? እንደ አማኝ የእኛስ ኃላፊነት ምንድ ነው?**
6. **ከዚህ በመነሳት በአሁን ወቅት የቆላስይስ ጥናት ማጥናት ለምን አስፈለገ?**
7. **ወደ ፊት ላለው የቆላስይስ ጥናት ዛሬ እንጸልያለን።**

# ጥናት ሁለት
# የቆላስይስ መጽሐፍ መግቢያ
# (ክፍል አንድ)
# የንባብን ክፍል፦ ቆላ 1:1-2

***ዓላማ***

የቆላስይስን መልዕክት ለማጥናት የሚረዱ መንደርደሪያ ነጥቦችን መዳሰስ ይሆናል።

***መግቢያ***

የቆላስይስ መልዕክት አጭር ከሚባሉት መልዕክቶች (አራት ምዕራፎች ብቻ ያሉት) አንዱ ቢሆንም፣ ግን በውስጡ ታላላቅ **የክርስትና አስተምህሮቶችን የያዘ፣ ታላላቅ አሳሳች የሀሰት ትምህርቶችን እና ፍልስፍናዎችንና ልማዶችን የሚገልጥ** መልዕክት **ነው**። የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ መጠን፣ በውስጡ ያለውን እውነት ጠንቅቀን እንድንመረምር እና እውነቱን አውቀን እንድንኖርበት ተጠርተናል። ስለዚህም በሚቀጥሉት ጥቂት ሳምንታት ይህንን መልክዕት በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሕብረት ውስጥ እናጠናለን።

ይህንን ለማድረግ እንዲረዳን ዛሬ የመልዕክቱን የመጀመሪያ ሁለት ቁጥሮች በመመልከት የመልዕክቱን ጸሐፊና ተቀባዮች እንዲሁም መጽሐፉን ለማጥናት የሚረዱ መንደርደሪያ አሳቦችን እንመለከታለን።

***<u>ትንታኔ/ማብራሪያ፦</u>***

**ቆላ.1፡1-2** ባለው ክፍል የመልዕክቱን ባለቤት፣ የመልዕክቱን ተቀባዮች እንዲሁም ለተቀባዩቹ የተላከውን ሰላምታ እናገኛለን። የመልዕክቱ ጸኃፊ ራሱን **"ጳውሎስ"** በማለት ነው የገለጸው። ምንም እንኳን ከዚህ በመነሳት የመልዕክቱ ጸሐፊ ጳውሎስ መሆኑን ብናውቅም፣ ይህንን እውነት የሚጠረጥሩ ምሁራን እንዳሉ ግልጽ ነው። ሆኖም ግን በዚሁ በቆላስይስ መጽሐፍ **ውስጥ ያሉ ማስረጃዎች** (Internal evidences) እንዲሁም ከመጽሐፉ **ውጪ ያሉ ማስረጃዎች** (External evidences)[2] የሚያመላክቱን ጸሐፊው በእርግጥ

[2] ለተጨማሪ ዕውቀት በዚህ ጥናት መጨረሻ ገጽ መመልከት ይቻላል

ሐዋርያው ጳውሎስ መሆኑን ነው። ለምሳሌ ከመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ማስረጃዎች ለመጥቀስ ያህል ጳውሎስ ጸሐፊው እኔ ነኝ ከማለቱ ሌላ፣ የአናሲሞስ ወደ ቆላስይስ መመለስ (ቆላ.4፡7-9፤ ፊል. 10-11)፣ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ የላኩት ሰዎች ስም ዝርዝር (ቆላ.4፡10-14፤ ፊል. 18-24)፣ የእስር ቤት መልዕክቶች ሲጻፉ የጢሞቴዎስ አብሮ መገኘት (ፊልሞ 1፡ 1 ቆላ. 1፡1፤ ፊልጵ. 1) እንዲሁም በቆላስይስ እና በፊልሞና መልዕክቶች ውስጥ የአግሪጳ መጠቀስ (ቆላ. 4፡17፤ ፊል. 1-3) በቂ ማስረጃዎች ናቸው። በተለይም ቆላ.4:10-11 ስናይ መልዕክቱ ከእስር ቤት የተላከ መልዕክት መሆኑን ያሳያል። ፊልጵስዩስ፣ ፍልሞና፣ኤፌሶን እና 2ኛ ጢሞቴዎስም እንዲሁ ከሮሜ እስር ቤት የተጻፉ መል ዕክቶች ናቸው። ከዚህም ባሻገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ በቤተክስቲያን ታሪክ የተነሱ ታላላቅ ሰዎች ይህ መልዕክት በጳውሎስ መጻፉን ይመሰክራሉ።

ቅዱስ ጳውሎስ ራሱን ሲያስተዋውቅ ስሙን ከመጥቀስ ባሻገር **"በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ"** መሆኑንም በመጥቀስ ነው። ጳውሎስ ሐዋሪያነቱ ለክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ነገር ግን ይህ ሐዋሪያነት በገዛ የግል ፈቃድ ወይም በአገልጋዮች ሹመት የተገኘ ሳይሆን በቀጥታ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተሰጠ ሹመት ነው (ገላ 1:1-2 ያለውን ያወዳድሩ)። ይህ የመልእክቱን እና የአገልጋይነቱን ሙሉ ሥልጣን ያመለክታል። መልዕክቱ ከሐዋሪያ በመምጣቱ የቆላስይስም አማኞች ሆኑ እኛ ዛሬ ስናነበው አንድ ጳውሎስ ከሚባል ግለሰብ እንደመጣ ሳይሆን ከእግዚአብሔር እንደመጣ መልዕክት ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልዕክት በሚጽፍበት ጊዜ እስር ላይ ነበር (ቆላ፡ 4:10-11)። ከላይ እንደተጠቀሰው ከኤፌሶን፣ ከፊልጵስዩስ እና ከፊልሞና መልዕክቶች ጋር አንድ ላይ የእስር ቤት መልዕቶች ተብሎ የሚመደበውም ከእነዚህ መልዕክቶች ጋር በአንድ ሰሞን ከመጽፉ ባሻገር ሐዋርያው በጊዜው በእስር ላይ የነበረ በመሆኑ ነው። የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ ላይ እንደምናገኘው ጳውሎስ በአገልግሎቱ ጊዜ በኢየሩሳሌም፣ በቂሣሪያና በሮም ታስሯል። ሆኖም ይህንን መልዕክት የጻፈው በሮም ሁለት አመት ገደማ እስር ላይ በነበረበት ጊዜ የሚለው ከሌሎቹ ይልቅ ተአማኒነት ያለው ነው። በመሆኑም ጸሐፊው ይህንን መልዕክት የጻፈው በ61 እስከ 63 ዓ/ም ባለው ጊዜ ነው።

ከጸሐፊው ጋር **“ጢሞቴዎስም ወንድሙ”** አብሮ ተጠቅሷል። ይህ ማለት ጢሞቴዎስም በመልዕክቱ ጽሁፍ ውስጥ ድርሻ አለው ማለት አይደለም።
ነገር ግን ጳውሎስ በሄደበት ሁሉ አብሮት እንዲወጣ ጢሞቴዋስን ከጠየቀው ጊዜ አንስቶ (ሐዋ 16:3) የማይለይ ታማኝ አገልጋይ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከጳውሎስ ጋር አብሮ
ወንድም ነው (2ኛ ቆሮ 1:1፣ ፊል 1:1፣ ፊልሞ 1:1 እንዲሁም 1ኛ እና 2ኛ ተሰ.ን ያወዳድሩ)

ጳውሎስ ራሱን እንዳስተዋወቀው መጠን የመልዕክቱንም ተቀባዮች **“በቆላስይስ ለሚኖሩ፣ በክርስቶስ ለሆኑ ቅዱሳን እና ታማኝ ወንድሞች”** (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) ሲል ያስተዋስቃል። አማኞቹ ነዋሪነታቸው በቆላስይስ ከተማ ነው። የቆላስይስ ከተማ ትገኝ የነበረው፣ የሮማ ቅኝ ግዛት በነበረችው በኤሽያ ግዛት፣ ፍርግያ በሚባለው አውራጃ ውስጥ ሲሆን፣ በጊዜው፣ ሄሪያፖሊስ እና ሎዶቂያ የሚባሉ ታላላቅ ከተሞች በአቅራቢያዋ ነበሩ። መልዕክቱ በተጻፈበት ዘመን፣ የቆላስይስ ከተማ እየወደቀች የነበረች ብትሆንም፣ ለሁሉም የሚያስፈልገው ወንጌል ግን ወደ ከተማይቱ መግባት ችሏል (ቆላ. 1፡6) ። ቆላስይስ በአሁኑ ጊዜ ቱርክ ትገኛለች።

**“በቆላስይስ ለሚኖሩ፣ በክርስቶስ ለሆኑ ቅዱሳን እና ታማኝ ወንድሞች”** የሚለው አገላለጽ የመልዕክቱ ተቀባዮች ሁለት አድራሻ እንዳላቸው ያስገነዝበናል። በአንድ በኩል ምድራዊ አድራሻ አላቸው። የሚኖሩት ቆላስይስ በሚባል ከተማ ውስጥ የከተማይቱን ህግና ደንብ እየተከተሉ ነው። በሌላ በኩል መንፈሳዊ አድራሻ አላቸው። በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ ቅዱሳን እና የታመኑ ወንድሞች ሆነው የክርስቶስን ህግ እና ደንብ እየተከተሉ ነው።

በአህዛብ ምድር፣ በቆላስይስ ከተማ ቅዱሳን እና ታማኝ ወንድሞች እንዴት ሊገኙ ቻሉ የሚለው ነገር ለአንዳንዶች የሚያመራምር ጥያቄ ነው። ጳውሎስም ሆነ ሌሎች ሐዋሪያት ከተማ መጥተው ወንጌልን እንደሰበኩ የሚናገር ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም። ጳውሎስ እንዲያውም በዚህች ከተማ ያሉትን አማኞች በአይን እንዳላያቸው ገልጿል (ቆላ 2፡ 1)። ሆኖም ግን ሐዋርያው

ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ወደ ሁለት አመት ገደማ በቆየበት ወቅት (ሐዋ 19:10) በእስያ ዙሪያ የነበሩት ከተሞች **<u>ወንጌልን በሰሙበት ጊዜ ኤጳፍራ የሚባል ሰው ወንጌልን ከጳውሎስ ሰምቶ በቆላስይስ ከተማ ቤተክርስቲያኗን ሳይመሰርት እንዳልቀረ ይታመናል (ቆላ 1:6-7)።</u>** ይህ መልዕክት በተጻፈበትም ጊዜ ስለ ቤተክርስቲያኒቷ ወሬውን ለጳውሎስ ያመጣውም ይኸው ኤጳፍራ ነው (ቆላ 1:7-8, ቆላ 4:12)።

**የመወያያ ጥያቄዎች (ቆላ 1:1-2 በማንበብ)**

1. **ቆላ 1:1-2 በማንበብ ስለ መልዕክቱ ጸኃፊ እና ተቀባዮች** የተገለጸው እንዴት ነው?
2. በተለይም **ቆላ.4:10-11** በማንበብ ስለ መልዕክቱ ምን እንማራለን? (ሐዋርያው ይህንን መልዕክት የጻፈው የት ሆኖ ነው ከዚህስ ምን እንማራለን)።
3. **ቆላ 1:1ን በማንበብ ስለ ሐዋርያው ጥሪ እና አገልግሎት ምን ያስተምረናል (ሐዋ 9:15-16፣13:1-3 ማንበብ እንችላለን)።**
4. **በቆላ 1:2 እና 3:1 መሠረት የቆላይስይስ መልዕክት ተቀባዮች ስንት አድራሻ እንዳላቸው ያስረዳል? ከዚህስ ምን እንማራለን?**
5. ቆላ 1:7,4:12 በማንበብ በቆላስይስ ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌል የመሰከረው ወይም ቤተ ክርስቲያን የተከለው ማን ነው? ከዚህስ ምን እንማራለን?
6. ከዚህ ጥናት በእግዚአብሔር መንግስት አብሮ ስለ ማገልገል ምን ያስተምረናል?
7. በአጠቃላይ ከዛሬው ጥናት ምን ተማርን? አናካፍል።

***መደሚደሚያ፡-***

**የቆላስይስ መልዕክት ዘላለማዊ የህይወት መርሆች ቢኖሩትም በአንድ ወቅት በቆላስይስ ከተማ እና አከባቢው ለሚኖሩ አማኞች በእግዚአብሔር በተጠራው በሐዋርያው ጳውሎስ የተጻፈ መልዕክት መሆኑን እንገነዘባለን።**

## ጥናት ሶስት

## የቆላስይስ መጽሐፍ መግቢያ

## (ክፍል ሁለት)

## የንባብን ክፍል፡- ቆላ 1፡1-2፣ (ቆላ. 2፡4, 8-20)

**ዓላማ**

የቆላስይስን መልዕክት ለማጥናት የሚረዱ መንደርደሪያ ነጥቦችን መዳሰስ ይሆናል።

**መግቢያ፡-**

የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት የተለያዩ ዓይነት **የአጻጻፍ ዘይቤዎች** (styles of writings) እንዳሏቸው ግልጽ ነው። ለምሳሌ የህግ፣የታርክ፣የቅኔ፣የትንቢት፣ ደብዳቤ እና ወዘተ ናቸው። የሐዋርያው ጳውሎስም መልዕክቶች የራሳቸው የሆነ የአጻጻፍ ዘይቤ (styles of writings) አለው:: መልዕክቶቹን የጻፈው በዳብዳቤያዊ ይዘት (Style) ነው፤ማለትም የጸሐፊው ስም፣የተቀባይ ስም፣ ሰላምታ፣ጸሎት/ምስጋና/፣ዋናው መልዕክት (body) እና መደምደሚያው (ቡራኬ-Doxology) ያጠቃለለ ይሆናል። የቆላስይስ መልዕክትም ይህንኑ መዋቅር የተከተለ ነው። በዚህ ጥናት በቆላ 1:1-2 እነዚህን ነገሮች እና የመልዕክቱን ታሪካዊ አውዱን (hisorical context) እናያለን።

**<u>ትንታኔ/ማብራሪያ</u>**

### በቤተ ክርስቲያኒቱ የነበረው ችግር

የቆላስይስን መጽሐፍ በአንክሮ ስናጠና በቤተክርስቲያኒቱ ዙሪያ ስለነበረው ችግር የምንረዳው አንድ ነገር ቢኖር፣ አማኞቹን ከትክክለኛው የክርስትና እምነት ጎዳና ለማውጣት ያንዣበበ የስህተት ትምህርት መኖሩን ነው **(ቆላ. 2፡4፣ 8-20)** ። ፍልስፍና፣ልምድ፣ህግ፣ወግ እና ሌሎችም ችግሮች በከተማይቱ እና በቤተ ክርስቲያንቱም ሰርጎ ገብቶ እንደነበር ይታወቃል። ይህንን ችግር ኤጳፍራ ለሐዋርያው የነገረው ይመስላል።

ሆኖም ግን ይህ ትምህርት በዘመኑ ከነበሩት ኑፋቄዎች የትኛው እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ሌላ ጽሑፎች ስለማይናገሩ፣ የስህተት ትምህርቱን ማንነት/ምንነት ለመለየት በመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ዘንድ የተለያየ ጥናት ቢደረግም፣ በአንድ ድምጽ ለኑፋቄው ስያሜ መስጠት አስቸጋሪ ሆኗል። ቢሆንም ግን <u>**ኑፋቄው የሚያስተምራቸው አንዳንድ አሳቦች በዚህ መልዕክት ውስጥ የተንጸባረቁ በመሆኑ፣ ምን ያህል አደገኛ እንደነበረ መረዳት እንችላለን።**</u>

## ሀ. ኑፋቄው ያቀፋቸው ከባድ ትምህርቶች ነበሩ።

ኑፋቄ (heresy, unorthodoxy, heterodox) ማለት በከፊል አምኖ በከፊል መካድ ማለት ነው። ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛ አስትምህሮ የሚቃወም ትምህርት ነው። ኑፋቄ ምንጩ የተለያዩ ነገሮች ሊሆኑ ይችላሉ።

1. ፍልስፍና አዘል ትምህርት ነበረበት። ፍልስፍና በራሱ ነውር ባይኖረውም፣ የዚህኛው ፍልስፍና ችግር እንዲኖረው ያደረገው፣ በአለማዊና ከንቱ በሆኑ ነገሮች ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው (ቆላ 2፡8)።
2. ሰዎችን አስሮ የሚይዝ ብዙ ሥርዓቶችን ያስተናገደ ትምህርት ነው (ቆላ. 2፡ 11፣14፣16፣17)።
3. የመላዕክትን አምልኮ የሚያስተምርና፣ መካከለኛ እንደሆኑ የሚያውጅ ነው (ቆላ.2፡15፣18፣ 19)።
4. የእምነቱ ተከታዮችን ወደ ብሕትውና ወይም ምነና (ascetic) የሚገፋፋ ትምህርት ነው (2፡20-23) ።
5. ባጭሩ እግዚአብሔርን ለመምሰል እና ወደሱ ሙላት ለመድረስ መንገዱ ፍልስፍና፣ ሕግጋትን መጠበቅ፣ ብሕትውና፣ ወይንም የመላዕክት አምልኮ የመሳሰሉት ናቸው የሚሉ የተለያዩ ኑፋቄዎች ብቅ ብቅ ብለዋል።

## ለ. ኑፋቄው የተለያዩ እምነቶች እና ፍልሰፍናዎች ድብልቅ (Syncretism) ነበር።

1. ከይሁዲነት አስተምህሮ ወስዶ ያቀፋቸው ትምህርቶች አሉ (2፡11፣ 16) ፡፡
2. ከባዕድ አምልኮ (Paganism) ወስዶ የሚያንጸባርቃቸው አስተምህሮዎች አሉት፡፡ ይህ የባዕድ ትምህርት በአብዛኛዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ዘንድ ኖስቲሲዝም (Gnosticism) ከተሰኘ ዕምነት የተወሰተደ ነው ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህ የኖስቲሳዊያን ትምህርት ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን የሚቃረኑ አስተምህሮችን የያዘ ሲሆን፣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የተወሰኑት ናቸው፡፡

**I. ቁስ አካላዊ ነገሮችን (matter) በተመለከተ**

1.1 ቁስ አካላዊ ነገሮች በሙሉ በራሳችው ክፉና የርከሱ ነገሮች ሲሆኑ፣ መንፈስ እና መንፈሳዊ የሆኑ ነገሮች በሙሉ በራሳቸው ቅዱስ እና ንጹህ ናቸው፡፡

1.2 እግዚአብሄር ቅዱስ በመሆኑ ርኩስ የሆኑትን ቁስ አካላት፣ አለማትንም ጨምሮ፣ እሱ አልፈጠራቸውም፡፡ አለማት የተፈጠሩት በእግዚአብሔር እና ቁስ አካላዊ በሆኑ ፍጥረታት መካከል ካሉ መናፍስት (Emanations/eons) ውስጥ ርኩስ የሆነውን አካል ለመፍጠር የሚያችል፣ በደርጃ ከመንፈሳዊነት ትንሽ ዝቅ ባለ ፍጡር ነው፡፡

1.3 . የሰው ሰውነት፣ ቁስ አካል እንደመሆኑ መጠን፣ በራሱ የረከሰ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ የዕምነቱ ተከታዮች ሰው እንዴት መኖር እንዳለበት በሚሰጡት ትምህርት ሁለት ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡

- ርኩስ ከሆነው አካል ለመዳን ሰው ብሕትውናን ሊለማመድ ይገባል (Ascetism)፡፡
- የሰው እውነተኛ ማንነት፣ ነፍስና መንፈሱ ስለሆነ በሥጋው የሚሰራው ነገር ምንም ችግር የለውም (Licentious)፡፡

## II. ክርስቶስን በተመለከተ

ቁስ አካል በራሱ የረከሰ እንደሆነ ለሚያምኑት ኖስቲሳዊያን፣ የክርስቶስን ሥጋ ለብሶ መምጣት (ተሰገዎ) ለመቀበል በጣም የሚያስቸግር ነው፡፡ ስለዚህ ስለ ክርስቶስ ማንነት በሚሰጡት ትምህርት ሁለት የተለያየ ኣመለካከት አላቸው፡፡

2.1 የመጀመሪያዎቹ ክርስቶስ እውነተኛ ሰው አልነበረም እንዲያው ሰው ይመስል ነበር ይሉ የነበረ ሲሆን አመለካከታቸው ዶሴቲዝም የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡[3]

2.2 ሌላኛዎቹ፣ ከመጀመሪያም ኢየሱስ ሰው ነበረ፣ በኋላ አምላካዊ ባህሪይ ያለው ክርስቶስ፣ ኢየሱስ ሲጠመቅ ወርዶበት "ተዳበለ" ብለው ያስተምሩ የነበረ ሲሆን፣ አመለካከቱ የትምህርቱ አቀንቃኝ በነበረው ሰሬንቲዩ ስም ሴሬንቲያኒዝም የሚል ስም ተሰጥቶታል፡፡[4]

**ከዚህም ባሻገር፣ በእግዚአብሔርና በፍጥረታቱ (ዓለማት) መካከል ያለው መካከለኛ (አማላጅ) ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ብዙ መንፈሳዊ አካላት አሉ ብለው ያምናሉ፡፡**

## III. ጥበብን/ እውቀትን በተመለከተ

- ድነት የሚገኘው በእውቀት/ጥበብ ነው፡፡
- ይህ እውቀት የሚገኘው በመማር ሳይሆን፣ በመመነን፣ እንደ ጥንቆላና ኮከብ ቆጠራ ዓይነት፣ አለማዊ ልማዶች ውስጥ በመሳተፍ ነው፡፡

የዚህን የዕውቀት ሀብት ለማግኘት፣ በኖስቲሳዊያን የፍልስፍና ትምህርት ውስጥ መግባት ያስፈልጋል፡፡

ከክርስትና እውነቶች የቀነጭባቸው ትምህርቶች አሉት፡፡ ትምህርቱ የክርስትናን ጭንብል ያጠለቀ ግን ውስጥ ውስጡን የአይሁድን እና የባዕድ አምልኮን አደባልቆ የያዘ ነው.

---

[3] አዲሱ መደበኛ ትርጉም የ1ኛ ዮሐ. መግቢያ ማጥኛ ጽሑፍ
[4] አዲሱ መደበኛ ትርጉም የ1ኛ ዮሐ. መግቢያ ማጥኛ ጽሑፍ

ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን ካስተዋወቀ እና የመልዕክቱን ተቀባዮች ከገለጸ በኋላ በቀጥታ ወደ ሰላምታው ይሄዳል። ሰላምታው አጭር እና ግልጽ ነው - "**ጸጋ እና ሰላም ለእናንተ ይሁን**" (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)። ጸጋ ለሰው የማይገባ ግን በነጻ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው። ይህ ጸጋ ለአማኝ የሚያስፈልገው ለድነት ብቻ ሳይሆን የዕለት ተዕለት የክርስትና ሕይወትንም በሚገባ ለመምራት የእግዚአብሔር ጸጋ አስፈላጊ ነው። ሰላም ኃጢአተኛ ሰው በክርስቶርስ ሞት እና ትንሳኤ በማመን ከእግዚአብሔር ጋር የሚመሰርተው እርቅ ነው። ይህን እርቅ የተቀበለ አማኝ "አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም" ልቦናውን እና አሳቡን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል። ሆኖም ግን እንዲህ አይነቱ ጸጋ እና ሰላም የሚገኘው "**ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ**" ብቻ ነው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከላይ በተገለጸው መሠረት የአጻጻፍ <u>**ዘይቤ**</u> ማለት ምን ማለት ነው? ይህን ማወቅ ለምን ይጠቅማል?
2. ከላይ በተገለጸው መሠረት <u>**ኑፋቄ ወይም መናፍቅ**</u> ማለት ምን ማለት ነው (ሐዋ 24:5 እና ቁ.14)?
3. የኑፋቄ ምንጩስ ምንድ ነው? ኑፋቄ የተለያዩ እምነቶች ድብልቅ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? ለዚህ እንድያግዘን ቆላ.2:8 እናብብ ።
4. ከላይ በተገለጸው ማብራሪያው መሠረት የኖስቲሳዊያን ትምህርት ምን እንደሆነ አብራሩ። <u>**ይህን የስህተት ትምህርት ማወቅ ለቆላስይስ መልዕክት ጥናት መሠረታዊ ነገር ነው።**</u>
5. የኖስቲሳዊያን አስተማሪዎች ስለ ክርስቶስ እና ስለ ድነት ምን እንደሚያስተምሩ ተነጋገሩ።
6. የስህተት ትምህርቶች ትክክል ላለመሆናቸው መሠረታዊ መለኪያ ምንድ ነው?
7. እነዚህ ትምህርቶች በዚህ ዘመን አሉ ብላችሁ ታስባላችሁ? ካለ አብራሩ

8. ዛሬ የስህተት ትምህርቶችን እየተቃወመን እንጸልያለን?

***መደምደሚያ፡-***

ባጭሩ የቆላስይስ መጽሐፍ በሐዋሪያት ዘመን በቆላስይስ ከተማ ለነበሩት አማኞች በሐዋርያው ጳውሎስ የተጻፈ መልዕክት ነው። ሐዋርያው በጊዜው ምንም እንኳ በእስር ላይ የነበረ ቢሆንም ከራሱ ይልቅ በዓይን ላላያቸው አማኞች አስቦ የጻፈላቸው ደብዳቤ ነው። በዚህም መልዕክት ወደ እግዚአብሔር ሙላት ያደርሳሉ የተባሉትን የሐሰት መላ ምት ትተው፣ እና በክርስቶስ ብቻ ሙሉ እና ብቁ መሆናቸውን አምነው በእርሱ እንዲተከሉ ይመክራቸዋል።

## ጥናት አራት
## በሰማይ ስላለን ተስፋ እግዚአብሔርን ማመስገን
## የንባብን ክፍል፦ ቆላ 1:3-8

### ዓላማ

ተስፋ ያለው ሕዝብ በመሆናችን፣ ተስፋ እንዳለው ሰው እግዚአብሔርን በማመስገን እና በጸሎት በመትጋት መንፈሳዊ ፍሬን እያፈራን እንድንኖር ማሳሰብ

### መግቢያ

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰላምታውን ካበቃ በኋላ ወደ ምስጋና፣ ጸሎትና ወደ መልዕክቱ ዋና ክፍል ይሄዳል። ባለፈው ሳምንት፣ ለዚህ መልዕክት መንደርደሪያ የሆኑ አሳቦችን ስንመለከት ጸሐፊው ጳውሎስ እንደሆነ፣ የመልዕክቱም ተቀባዮች በቆላስይስ ከተማ የሚገኙ አማኞች እንደሆኑ ተመልክተናል (ቆላ 1:1-2)። ጳውሎስ ለነዚህ አማኞች ሰላምታውን ካቀረበ በኋላ፣ ከቁ 3-14 ባለው ክፍል እንደሚጸልይላቸው ይናገራል። ይህ ደግሞ በሌሎች መልዕክቶችም የሚያደርጋቸው ልማዶቹ ናቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ "ስንጸልይ" (1:4)፣ "...እየለመንን ስለእናንተ ጸሎትን አልተውንም" (1:9)፣ "እንለምናለን" (1:12) የሚሉት ቃላቶች፣ ክፍሉ እነጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የሚያደርጉትን ጸሎት ያመለክታሉ። ሆኖም ይህንኑ ክፍል በሁለት መክፈል እንችላለን። **<u>ከቁ 3-8 የምሥጋና ክፍል ሲሆን 9-14 ያለው ደግሞ የልመና ክፍል ነው። በዛሬው ጥናታችን የምሥጋናውን ክፍል እናይና በሚቀጥለው ጥናት የልመናውን ክፍል እንዳስሳለን።</u>**

### <u>ትንታኔ (ማብራሪያ)</u>

ሐዋርያው የምሥጋናውን ክፍል ሲጀምር "**ስለ እናንተ ስንጸልይ ... ሁልጊዜ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን**" (ቁ. 3) ይላል። በዚህም ጳውሎስ ምንም እንኳ ምዕመናኑን በአይነ ሥጋ ባያያቸውም ግን እንደሚጸልይላቸው ያስገነዝበናል። ምንድን ነው የሚጸልይላቸው የሚል ጥያቄ ከተነሳ፣ የሚጀመሪያው የጸሎቱ ክፍል ምሥጋና ነው። ስለ እነዚህ አማኞች እንዲያመሰግኑ

ምክንያት የሆናቸው ስለ ቆላስይስ ሰዎች የሰሙት መልካም ዜና ነው። እግዚአብሔርን የምናመሰግነው "**በክርስቶስ ኢየሱስ ስለ እምነታችሁ፣ ለቅዱሳምን ሁሉ ስላላችሁ ፍቅር ሰምተን**" ነው ይላል። በእርግጥ እነዚህ ሁለቱ ነገሮች (ማለትም እምነት እና ፍቅር) ድሮ ባእድ አምልኮ በሚያድርጉ ሰዎች መካከል መገኘታቸው ተአምር ነው። ይህ አይነቱ ፍሬ በእግዚአብሔር ካልሆነ በሰው ጥረት የሚገኝ አይደለም። እዚህ ጋር "እምነት" የሚለው ቃል የሚያመለክተን በክርስቶስ አምነው መዳናቸውን ብቻ ሳይሆን፣ ከድነት በኋላም በጌታ አምነው (ተማምነው) የሚኖሩትንም ኑሮ ነው። እንደዚህ አይነቱ ሕይወት ብዙ ዋጋን ያስከፍላል። እምነት በመከራ ስለሚፈተን የእምነት ሰዎች የሚባሉትም በአንደበታቸው እናምናለን ስላሉ ሳይሆን በሚያልፉበት መከራ ሁሉ ስለእምነታችው በመጽናታቸው ነው። የቆላስይስ ሰዎችም በክርስቶስ አምነው፣ የከፈሉት ዋጋ ባይገለጽልንም ግን በክርስቶስ ታላቅ እምነት አላቸው።

ፍቅርም እንደ እምነት በአንደበት ቃል ብቻ የሚገለጽ ሳይሆን በተግባር የሚገለጽ ነው (1ኛ ዮሐ 4:16-18)። ፍቅር፣ ያለንን ለሌለው ማካፈልን ይጠይቃል፣ ፍቅር የራስን ወደ ኋላ ትቶ ለሌላ ቅድሚያ መስጠትን ይጠይቃል፣ ፍቅር ስለሌላው ቢያስፈልግ ነፍስን መስጠት ይጠይቃል (1ኛ ዮሐ 4:16)። ገንዘብንና ራስን መውደድ እንደ ብልጥነት በሚቆጠርበት ዓለም ሌሎች ቅዱሳንን (ያውም ቅዱሳንን ሁሉ) መውደድ መቻል አስገራሚ ነገር ነው። በእርግጥም በቁ 8 ላይ እንደምናየው ይህ በመንፈስ ቅዱስ የሚሆን ፍቅር እንጂ በሰው የሚሆን አይደለም (ሮሜ 5:5 ያወዳድሩ)።

እነዚህ ሁለት የክርስቲያን መለያዎች በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን መገኘታቸው ልከኛ የክርስቲያን ሕይወት (Balanced Christian Life) እንዳላቸው ያመለክታል። ምክንያቱም ክርስቲያን በክርስቶስ ብርቱ እምነት ቢኖረው ግን ለሌሎች ፍቅር ባይኖረው ሕይወቱ መና ነው፤ ለዛም ነው "ተራሮችንም እስካፈርስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ፣ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ

ነኝ" (1ኛ ቆሮ 13:2) መባሉ። ደግሞም እውነተኛ እምነት የሚገለጠው በተግባር ነው (ያዕ 2:14-17)። በዚያው ልክ እምነት የሌለው ፍቅርም ዋጋ የለውም፣ ፍቅር ያለ እምነት ስሜት ብቻ ይሆናልና። "ክርስቲያን መንታ ሃላፊነት አለበት - ለክርስቶስ የተሰጠ መሆን አለበት እንዲሁም አብረውት ላሉት ሰዎችም የተሰጠ መሆን አለበት። በክርስቶስ ማመንና ሰዎችን መውደድ መንታ የክርስቲያን ሕይወት መሰሶዎች ናቸው።"[5]

በእምነትና በፍቅር የበረታችሁት "**በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ የተነሳ**" ነው ይላል። ይህ በሰው ዘንድ ሞኝነት ሊመስል ይችላል። ገና ለገና ያውም በሰማይ ተስፋ አለ ተብሎ ለክርስቶስ ዋጋ እየከፈሉ ለሌላው ቅድሚያ እየሰጡ መኖር ይከብዳል። ግን ሁለት ነገሮች እዚህ ጋር ሊጤኑ ይገባል። በመጀመሪያ ተስፋው የሰው ተስፋ ወይንም ቃል ኪዳን አይደለም። የሰውን ቃል ተስፋ አድርጎ መወሰን ትልቅ አደጋ አለው ሰው ቃሉን ሊለውጥ ወይንም ቃሉን መጠበቅ ላይችል ስለሚችል። ይህ የቆላስይስ ሰዎች ተስፋ ያደረጉበት ተስፋ የእግዚአብሔር ተስፋ ነው። የተስፋን ቃል የሰጠው እግዚአብሔር ደግሞ የታመነ ነው (ዕብ 11:11) ስለዚህም እሱ የሰጠን ተስፋ አያሳፍረንም (ሮሜ 5:5)። ሁለተኛ ይህ ተስፋ በሰማይ የተቀመጠ ተስፋ ነው። እዚህ ጋር በሰማይ ከተዘጋጀላችሁ ተስፋ ሲል "ከተዘጋጀላችሁ" ተብሎ የተተረጎመው ቃል ትክክለኛው ትርጉም "ከተቀመጠላችሁ" ወይንም "ከተጠበቀላችሁ" የሚል ነው (አዲሱ መደበኛ ትርጉምን ያወዳድሩ)።[6] እግዚአብሔር ለሚወዱትና ለሚያምኑበት የወሰነላቸው ወይንም ያስቀመጠላቸው ተስፋ አለ። እዚህ ክፍል ላይ ያ ተስፋ ምን እንደሆነ አብራርቶ ባይነግረንም ተስፋው በሰማይ የተቀመጠ በመሆኑ ሰው በምድር ላይ ተስፋ አድርጎ እንደሚያስቀምጠው ምድራዊ ነገር ብል የሚበላው፣ ዝገት የሚያበላሸው፣ እሳት አመድ የሚያደርገው፣ ነፋስ ጠርጎ የሚወስደው ተስፋ አይደለም። ተስፋው እርግጠኛ የሆነ፣ የማይጠፋ መፈጸሙም የማይቀር ነው። እንዲህ ያለው ተስፋ በሰዎች ዘንድ እምነትና ፍቅር ማምጣቱ እንግዳ ነገር

---

[5] William Barclay, *THE LETTERS TO THE PHILLIPIANS, COLOSSIANS AND THESSALONIANS* (Philadelphia, 1975), 105.

[6] በ1:5 ላይ"ከተዘጋጀላችሁ" ተብሎ የተተረጎመው αποκειμενην (አፖኬሜኔን) ከሚል የግሪክ ቃል ሲሆን ሲተረጎም እንደየአገባቡ "የተጠራቀመላችሁ"፣ "የተቀመጠላችሁ"፣" የተጠበቀላችሁ"፣ የሚጠብቃችሁ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል (ሉቃ 19:20፣ 2ኛ ጢሞ 4:8 እንዲሁም ዕብ 9:27ን ያወዳድሩ።

አይደለም። ለምሳሌ አብርሃም ታላቅ የእምነት ሰው የተባለው የተሰጠውን የተስፋ ቃል አምኖ እስከመጨረሻው በመጠበቁ እንደሆነ አይዘነጋም።

ይህ ሲባል የቆላስይስ ሰዎች ይህንን ሰማያዊ ተስፋ ከየት አመጡት የሚል ጥያቄ ማንሳት አይቀሬ ነው። ይህንን የተስፋ ቃል ራሳቸው አልፈለሰፉትም ወይንም ከሰማይ መላዕክ አላመጣላቸውም። ጳውሎስ በግልጽ "**ስለዚህ ተስፋ በወንጌል እውነት ቃል አስቀድማችሁ ሰማችሁ**" በማለት ምንጩ ወንጌል እንደሆነ ያስገነዝበናል። ወንጌል በሮሜ 1:3-5 ባለው ክፍል እንደተገለጸው ክርስቶስ ኢየሱስን የሚሰብክ የምስራች ነው። በኃጢአት ያለ ተስፋ የጠፋው ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ መፍጠር የሚችልበት የተስፋ መንገድ መከፈቱን ያበስራል። ይህ የምስራች ዛሬ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንደምንችል ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ጌታ ክርስቶስ አንድ ቀን እንደሚመጣ፣ እኛም እንደምንለወጥ፣ ፍጥረት እንኳ ሳይቀር እፎይ እንደሚል፣ እግዚአብሔር ለልጆቹ ያስቀመጠውን ርስት እንደምንቀበልና ከእርሱም ጋር ለዘላለም እንደምንኖር ያበስራል። ወንጌል የተስፋ መልዕክት ነው! ስለዚህም ሰዎች ወንጌልን አንሰማም ብለው ሲገፉት ተስፋ መቁረጥ በበዛበት አለም ውስጥ የመጣላቸውን የተስፋ ጭላንጭል ነው የሚያጠፉት።

እንግዲህ ከቁ 3-5 ባለው ክፍል ይህ የጳውሎስ ደብዳቤ የሚነገረን ነገር፣ አስቀድሞ ወንጌል በቆላስይስ በተሰበከ ጊዜ በሰሚዎቹ ዘንድ ተስፋን እንደዘራና ይህ ተስፋ እምነትንና ፍቅር በመካከላቸው እንዳበዛ ነው። ቀጥሎ ባለው ቁጥር (ቁ. 6) የዚህን የወንጌል ጉልበት ይዘግባል።

በመጀመሪያ ወንጌል ወደ ቆላስይስ ሰዎች የመጣው ልክ በሌላው የዓለም ክፍል እንደሚያደርገው ነው- "**ይህም በዓለም ሁሉ ደግሞ እንዳለ ወደ እናንተ ደርሷል**"። የወንጌል በቆላስይስ ከተማ መግባት እንግዳ ነገር አይደለም - ይህ የወንጌል ጸባይ ነው። ወንጌል እንደ ሰደድ እሳት ነው - ይዛመታል።

ነገሩ “ሲያጠፉት ይነዳ፣ ሲያፍኑት ይብሳል” ተብሎ እንደተዘመረው ነው። አንድ ቦታ የበቀለው ወንጌል እናጥፋህ ቢሉት አይጠፉም ይልቅ ግን እየተዛመተና እየባሰ አገር ምድሩን እያጥለቀለቀ ይሄዳል። ስለዚህም በሌላው ዓለም አስቀድሞ የተሰማው ወንጌል ሲዛመት ቆላስይስ ደረሷል።

በመቀጠል ይህ ወንጌል በየቦታው መዳረስ ብቻ ሳይሆን በደረሰበት ያድጋል ደግሞም ፍሬን ያፈራል። “**የ’እግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት ከሰማችሁበት እና ካወቃችሁበት ቀን ጀምሮ፣ በእናንተ ደግሞ እንዳለ (*እንደሚያደርገው*) እንዲህ በዓለም ፍሬ ያፈራል ያድግማል።*”* ከፍ ብለን እንዳየነው፣ የቆላስይስ ሰዎች በወንጌል የሚሰበከውን ተስፋ አስቀድመው ሰምተዋል። ይህም የሰሙት እውነት በመካከላቸው ፍሬን አፍርቶ፣ የእምነታቸውና የፍቅራቸው ብርታት የሚወራለት ሆኗል። አገልጋያቸው ኤጳፍራ ይህንን ይመሰክራል **(ቁ. 8**) እነ ጳውሎስም ይህንን ሰምተዋል **(ቁ. 3-5)።** ጳውሎስ በዚህ ክፍል ሲነግረን ግን የሚያሳስበን በቆላስይስ ወንጌል ማደግና ማፍራት የጀመረው ወንጌልን ከሰሙበት ቀን አንስቶ መሆኑን ነው። ግን ወንጌል ይህንን አስገራሚ እድገትና ፍሬ ያሳየው በቆላስይስ ብቻ አይደለም ነገር ግን ልክ በቆላስይስ እንደሚያድገውና እንደሚያፈራው እንዲሁ በዓለም ዙሪያ ይህንኑ ተአምር እየሰራ አለ። ወንጌል ልክ እንደ ዘር ነው! ዘር ሲዘራ ይበቅላል … ያድጋል … ብሎም ፍሬን ያፈራል ግን እዚያ ጋር አያቆምም ፍሬው ሌላ ችግኝ ይዞ ብቅ ይላል። ወንጌልም እደዚያው ነው። እኛም ወንጌልን ለማዳረስ ይህ እውነት ጉልበት እንዲሆነን ይገባል። ወንጌልን ስንሰብክ ያ ሞኝነትና ትንሽ የመሰለው ወንጌል ጉድና ተአምር እየሰራ ሰወችን እያዳነና ፍሬን እያፈራ እኛኑ ጉድ ያሰኘናል።

በቁ. 7 ላይ ጳውሎስ ይህንን ወንጌል እንዴት የቆላስይስ ሰዎች ሊሰሙት እንደቻሉ ያስረዳል። በእርግጥ ወንጌል ከላይ እንዳልነው እንደ ሰደድ ከቦታ ቦታ እየተዛመተ የሚሄድ የተስፋ መልዕክት ነው። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ይህ መልዕክት በሰዎች እንዲሰበክ ይፈልጋል። በዚህም መሰረት ይህንን ወንጌል ወደቆላስይስ ሰዎች እንዴት እንደመጣ ጳውሎስ ያስረዳል።፡”**ከተወደደ ከኛም ጋር ባርያ ከሆነው ከኤጳፍራ እንዲህ ተማራችሁ፣ እርሱም ስለ እናንተ ታማኝ**

**የክርስቶስ አገልጋይ ነው።**” በመጀመሪያ ወንጌል ኤጳፍራን ራሱን አግኝቶታል፣ የክርስቶስ ታማኝ አገልጋይ፣ የተወደደ ባርያ ሊሆን የበቃው ወንጌል እሱን ስለነካው ነው። ይህ የሆነው ምናልባት ጳውሎስ በኤፌሶን ከተማ ሁለት አመት ገደማ በቆየበት ጊዜ፣ ኤጳፍራ ባጋጣሚ ኤፌሶን ሄዶ ወንጌልን ሰምቶ ሊሆን ይችላል (ሐዋ 19:10 ይመልከቱ)። ኤጳፍራን ታማኝ፡የክርስቶስ አገልጋይ ከነጳውሎስ ጋርም አብሮ የሚደክም ተወዳጅ ባርያ ያደረገው ይህ መልዕክት በሚጻፍበት ጊዜ ለጳውሎስ በሚሰጠው ግልጋሎት ብቻ ሳይሆን ወንጌልን በታማኝነት ለቆላስይስ ማድረሱ ነው። ይህንን ድንቅ የወንጌል ተስፋ መስማት የቻሉት ኤጳፍራ ታማኝ በመሆኑ ነው። ይህም ወንጌል እንዲሰራጭ እኛም ሃላፊነት እንዳለብን ያስገነዝበናል። ምንም እንኳ ወንጌል በራሱ ጉልበት ቢኖረውም፣ ያለ ወንጌል ሰባኪ ክርስቶስን ያወቁ ሰዎች ቢኖሩም፣ ግን እግዚአብሔር ወንጌል በኛ ሕይወት ውስጥ የሰራውን እንድንመሰክር ይፈልጋል፣ ሃላፊነትም ተሰጥቶናል።

በቁ. 8 ላይ ጳውሎስ ስለ ቆላስይስ አማኞች እውነተኛ ፍቅር ከማን እደሰማ ይገልጻል። ኤጳፍራ “**ደግሞም በመንፈስ ስለሚሆን ፍቅራችሁ አስታወቀን**” ይላል። ወንጌልን ወደ ቆላስይስ ያደረሰው እሱ ነው ወንጌሉም በመካከላቸው ያመጣውን ለውጥ የሚመሰክረው እሱ ነው።

እግንዲህ ጳውሎስ ስለ ቆላስይስ ሰዎች እግዚአብሔርም የሚያመሰግንበትን ይህንን ክፍል ስናይ በወንጌል የተሰጠን ተስፋ በሰዎች የሚያመጣውን እውነተኛ ለውጥ ያሳየናል። ለጳውሎስም የምሥጋናው ምክንያት ይህንን የለውጥ ፍሬ በቆላስይስ አማኞች ላይ ማየቱ ነው። የወንጌል ተስፋ ብርቱ የእምነትና የፍቅር ሰው አድርጓቸዋል። እምነታቸውና ፍቅራቸው የሚወራለት ሰዎችን የሚያነጋግር ሆኗል። ግን ይህ አይነቱ ለውጥና ፍሬ በቆላስይስ ውስጥ ብቻ የታየ ሳይሆን ወንጌል በደረሰበት ሁሉ እንደ ዘር እያደገ ፍሬን የሚያፈራ ነው። እኛም ዛሬ ይኸው የወንጌል ተስፋ አለን። በክርስቶስ ትንሳኤ ምክንያት ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፣ እድፈትም ለሌለበት ለማያልፍም ርስት ተጠርተናል (1ኛ ጴጥ 1:3-

5)። ግን ይህ ተስፋ በልባችን ትልቅ ስፍራ ይዞ እንደ ቆላስይስ ሰዎች በእምነትና በወገኖች ፍቅር እንዲሁም በመንፈስ ፍሬዎች እያደግን ይሆን?

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቆላ 1:3-4 በመመልከት የቆላስይስ አማኞች ጠንካራ ነገራቸው ምን እንደሆነ ተነጋገሩ? ምንስ እንማራለን?
2. ቆላ 1:5-6 መሠረት ይህ በወንጌል የሚሰበከው ተስፋ በሰዎች ህይወት ውስጥ የሚያመጣው ውጤት ምንድ ነው? 1ኛ ጴጥ 1:3-5።
3. የቆላስይስ ሰዎች እምነታቸው የጨመረው በሰማይ ከተጠበቀላቸው ተስፋ የተነሳ ነው። የወንጌል ተስፋ እንዴት ነው እምነታችንና ፍቅራችን እንዲበዛ የሚያደርገው?
4. ቆላ.1:6 በማንበብ መስማት፣መረዳት፣መሥራት፣ማፍራት.. ከሚሉ ሀሳቦች ምን እንማራለን።
5. ቆላ.1:7 ስናነብ የቆላስይስ ሰዎች ይህንን ድንቅ የወንጌል ተስፋ መስማት የቻሉት በማን አማካኝነት ነው? ከዚህ እኛ ለወንጌል ስላለን ኃላፊነት ምን እንማራለን?
6. እንደ ቆላስይስ ሰዎች በእምነትና በወገኖች ፍቅር እንዲሁም በመንፈስ ፍሬዎች የምናድገው ምንን ስንገነዘብ ነው።
7. ከዚህ የተነሳ በወንጌል የሚሰበከውን እወነተኛ ተስፋ ለሰዎች መናገር አስፈላጊ የሆነው ለምንድ ነው? በወንጌል ያልተደገፈ እውነተኛ ያልሆነ ተስፋ መስጠት እንችላለን? አዎን ካልን ምን?
8. **በዛሬው ጥናት መሠረት ይህንን በወንጌል የሚሰበከውን እውነተኛ ተስፋ ይዘን እንዳንቀመጥ ምን እናድርግ (እቅድ)?**

**መደምደሚያ፡-**

ተስፋ ለሰው ልጅ የሕይወት ጉልበት ነው። ያለ ተስፋ መኖር ተራራን እንደመግፋት ነው። እኛ ክርስቲያኖች ደግሞ እርግጠኛ የሆነ ሰማያዊ ተስፋ ያለን ሰዎች ነን። ይህ ተስፋ ይህንን ምድራዊ ኑሮ በደስታ እና እውነተኛ መንፈሳዊ ፍሬን እያፈራን እንድንንኖር ሊያበረታታን ይገባል።

# ጥናት አምስት

# በእግዚአብሔር ፈቃድ እውቀት እና ጥበብ ለመሞላት መጸለይ

# የንባብ ክፍል ፡ ቆላ 1:9-14

### ዓላማ

በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅና እንደፈቃዱ መመላለስ እንድንችል ስለ አካሄዳችን (እውቀት እና ጥበብ እንደሚገባን) መጸለይ እንደሚገባን ማስገንዘብ።

### መግቢያ

ብዙ ጊዜ ለጸሎት ስንበረከክ የጸሎታችን ትኩረት ለዚህ ምድራዊ ሕይወታችን ጎደለን የምንለው ነገር እንዲሟላልን ነው። ስለምንለብሰው፣ ስለምንበላው፣ ስለትምህርት፣ ስለቤተሰብ፣ ስለ ሥራ … ወዘተ። በእርግጥም ስለነዚህ ሁሉ መጸለይ ክፋትም ነውርም የለበትም። እንዲያውም ተገቢ ነገር ነው። **<u>ሁልጊዜ የምንዘነጋው ግን ስለ ክርስትና ሕይወታችን መጸለይ ነው።</u>** ጌታ ሆይ ሕይወቴን አስተካክለው፣ አንተ እንደምትወድው መኖር እንድችል ጉልበት ስጠኝ፣ ከኔ የምትፈልገውን እንዳውቅ እርዳኝ … የሚሉ ጸሎቶችን መስማት ብርቅ ነው። ሆኖም ግን በተቃራኒው ሊሆን የሚገባው ከምንም በላይ ትልቁ የጸሎታችን ርዕስ ሊሆን የሚገባው **<u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅና እንደ ፈቃዱ መኖር እንዲያስችለን መለመን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ጊዜ ቦታ እንደጸለየ ይታወቃል። ከእነዚህ አንዱ ታዋቂው በዮሐ ወንጌል 17 ተጽፎ ይገኛል። ክፍሉን እንድናነብ እናበረታታለን።</u>**

ጸሎታችን እንደእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለበት። የእግዚአብሔን ፈቃድ አውቀን እንደ ልቡ ፍላጎት መኖር መቻል ዘላለማዊ ነው። በመሆኑም ይህ ዓይነቱ ሕይወት ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣውም ዓለም ይጠቅማል **(1ኛ ጢሞ 4:8-9)**። ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ አማኞች በሚጸልይበት ቦታ ሁሉ የልቡ

ሸክም አማኞች የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀው እርሱን ደስ በማሰኘት ህይወት እንዲመላለሱ ነው፡፡

በዛሬው ጥናታችን ጳውሎስ ለቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ያቀረበውን ልመና በመመልከት የኛም የልብ ጩኸት የጌታን ፈቃድ ማወቅና ለጌታ ደስ በሚያሰኝ ሕይወት መመላለስ እንዲሆን እንደሚገባው እናያለን፡፡

## ትንታኔ/ማብራሪያ

ባለፈው ጥናታችን እንደተመለከትነው፣ ቆላ 1:3-14 ያለው ክፍል የሐዋርያው ጳውሎስን ጸሎት የዘገበበት ክፍል ነው፡፡ **ባለፈው እግዚአብሔርን ስለማመስገን ተመልተናል፡፡** በዛሬው ጥናታችን ከቁ 9 – 14 ባለው ክፍል የጳውሎስን የልመና ጸሎት እናያለን፡፡ በዚህ ክፍል ሐዋርያው ለቆላስይስ ሰዎች የሚያቀርበው ልመና ሁለት ነገሮችን ሲሆን፣ ሁለት ጊዜ "እየለመንን" (ቁ. 9) ወይንም "እንለምናለን" (ቁ. 12) በሚሉት ቃላት ተጠቅልለዋል፡፡ የመጀመሪያው ልመና "**የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፣ ስለእናንተ ጸሎትን አልተውንም**" የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው "**በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን**" የሚል ነው፡፡

***የመጀመሪያው ልመና "... እግዚአብሔር የፈቃዱን ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላችሁ ዘንድ"፡፡*** እዚህ ጋር የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ ሲል፣ ነገ ምን እንድለብስ ነው እግዚአብሔር የሚፈልገው? ማንን ነው ማግባት ያለብኝ? የት ትምህርት ቤት ልመዘገብ? የት አገር እንድኖር ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚሉት የየዕለት ጥያቄዎቻቸውን የሚመልስ ፈቃድ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር እንደ ክርስቲያን ከአማኞች የሚጠብቅባቸውን ክርስቲያናዊ አካሄድ እንዲያውቁ ነው፡፡[7] ይህ እውቀት የጭንቅላት ብቻ እውቀት ሳይሆን **"በመንፈሳዊ ጥበብ እና አእምሮ ሁሉ"** የሚታይ (የሚገለጥ) ነው፡፡ በሌላ አባባል ይህን የእግዚአብሔርን ፈቃድ እውቀት የተረዳ በመንፈሳዊ ጥበቡ እና

---

[7] Curtis Vaughan, *Colossians and Philemon* (Grand Rapids, 1980), p 28.

ማስተዋሉ ይታያል ማለት ነው። መንፈሳዊ ጥበብ ምንድን ነው ያልን እንደሆነ፣ ሥጋዊ ወይንም አለማዊ ያልሆነ፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ወይንም ሰማያዊ የሆነ ጥበብ ነው። ይህም በያዕቆብ 3:13 – 18 በሚገባ ተገልጿል። ምድራዊ የሆነው ጥበብ ትርፉ መራርነት፣ ቅንዓት፣ አድመኝነት ... ነው። መንፈሳዊው ጥበብ ግን ቅንነት፣ ትህትናን፣ እሺ ባይነትን፣ ምህረትን ... የምታስተምር ናት።

**መንፈሳዊ አእምሮስ ምንድን** ነው የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። በመጀመሪያ አእምሮ ተብሎ የተተረጎመው ቃል ማስተዋል ወይንም መረዳት ለማለት ነው (አዲሱ መደበኛ ትርጉም ያነጻጽሩ)። ይህ ማስተዋል ከላይ የተጠቀሰውን መንፈሳዊ ጥበብ አስተውሎ በእለት ተእለት ኑሮ በተግባር መተርጎምን ያሳያል። ለምሳሌ እንደ ክርስቲያን ሌላውን ወንድም ዝቅ ብሎ ማገልገል ትህትናም መንፈሳዊ ጥበብም ነው። ይህም ማስተዋል ደግሞ በተግባር በምድራዊ ነገር ሁሉ የምንበልጠውን ዝቅ ብለን ማገዝ ማለት ነው። እንግዲህ የጳውሎስ የመጀመሪያው ጸሎት የቆላስይስ አማኞች በክርስትና ሕይወታቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ አውቀው በጥበብ እና በማስተዋል እንዲኖሩ ነው።

**ሁለተኛው ልመና ለጌታ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን** የሚል ነው። ይህ ልመና ከመጀመሪያው ልመና ጋር የተያያዘ እና ከመጀመሪያው የሚቀጥል ነው። የጳውሎስ መሻት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁ ብቻ ሳይሆን በዚያ እውቀት መሰረት ለጌታ እንደሚገባ እንዲኖሩ ነው። እዚህ ጋር "**ለጌታ እንደሚገባ**" ተብሎ ወደ አማርኛችን የተተረጎመው <u>**በጌታ መጠን ልክ እንድትመላለሱ**</u> ለማለት ነው። ጌታ የሚጠብቅብን አካሄድ **"የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ ፍጹማን ሁኑ"** (ማቴ 5:48) ወይንም "እኔ ቅዱስ ነኝና ቅዱሳን ሁኑ" (1ኛ ጴጥ 1:15) የሚል ነው። ለምን ካልን ጳውሎስ እዚያው ላይ መልስ ሲሰጥ **"በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ"** እንድትችሉ ይላል። እንደ ክርስቲያን በዚህ ምድር ትልቁ ጥማታችን ሊሆን የሚገባው በሁሉ ጌታን ደስ ማሰኘት ነው (2ኛ ቆሮ 5:19)። ጌታን እንደዚህ በሁሉ ደስ ለማሰኘት አማኝ ከጌታ በሚጠበቅበት

መጠን ልክ ለሱ እንደሚገባው መኖር ይጠበቅብናል። ጳውሎስም ልመናው የቆላስይስ አማኞች አሁን ባላቸው መንፈሳዊ ሕይወት እንዲረጉ ሳይሆን ጨምረው በሁሉ ጌታን ደስ እያሰኙ ለእርሱ በሚገባ እንዲኖሩ ነው።

ጳውሎስ እግዚአብሔርን ደስ እያሰኙ ለጌታ እንዲሚገባ የሚኖሩበትን አራት ነጥቦች ያነሳል 1) "**በበጎ *ሥራ* ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ**" ፣ 2) "**በእግዚአብሔርም እውቀት እያደጋችሁ**" ፣ 3) "**እንደክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታቻችሁ**" እና 4) "**አብን እያመሰገናችሁ**" **ናቸው።** የመጀመሪያው በበጎ *ሥራ* ሁሉ ፍሬ ማፍራት ነው። ባለፈው ጥናታችን ወንጌል በዓለም ዙሪያ እንዲሁም በቆላስይስ ከተማ ፍሬን እያፈራ እንደነበረ ተመልክተናል። በቆላስይስ አማኞቹ በጌታ ያላቸው እምነት እንደጠነከረና ለወገኖች ያላቸው ፍቅር እንደበዛ አይተናል። አሁን ጳውሎስ በዚህ ብቻ ሳይሆን በበጎ *ሥራ* ሁሉ ፍሬን እንዲያፈሩ ያሳስባል። መቼም ፍሬና ስር የተለያዩ መሆናቸው በጣም ግልጽ ነው። ዛፍ ያለ ስር መኖር አይችልም ያለ ፍሬ ግን መኖር ይችላል። ልክ እንዲሁ አማኞቹ ያለ ፍሬ መኖር ይችሉ ይሆናል ግን ጌታን ደስ የሚያሰኝና ለሱ እንደሚገባ ለመኖር ፍሬን እንዲያፈሩ ይገባል። ከፍሬም ዓይነት አለው። መራራና መርዘኛ ፍሬ የሚያፈራ ዛፍ እንዳለ ሁሉ መልካም ፍሬም የሚያፈራ አለ፤ እዚህ *ጋ* ግን የተጠየቁት በበጎ *ሥራ* ሁሉ ፍሬን እንዲያፈሩ ነው። ይህ በጎ *ሥራ* የመንፈስ ፍሬ ተብለው በገላ 5:22-24 የተዘረዘሩትን የሚጨምር ነው።

ቅርንጫፍ ፍሬን ማፍራት እንዲችል ከግንዱ *ጋ*ር ጠንካራና ጤነኛ ግንኙነት እንዲኖረው ያስፈልጋል። ልክ እንዲሁ የቆላስይስ አማኞችም ሆኑ እኛ ዛሬ በበጎ *ሥራ* ሁሉ ፍሬ እንድናፈራ ካስፈለገ ከጌታ *ጋ*ር የጠበቀ ሕብረትና ግንኙነት እንዲኖረን ያስፈልጋል (ዮሐ 15:4)። አማኝ ከጌታ *ጋ*ር ሕብረት ከሌለው፣ ሕብረቱና ግንኙነቱ ከዓለም *ጋ*ር ከሆን፣ ፍሬውም አለማዊ ይሆናል።

**ሁለተኛው** በእግዚአብሔር እውቀት ማደግ ነው። እዚህ *ጋ* ጳውሎስ አማኞቹ እግዚአብሔርን በማወቅ እዲያድጉ ሲቀናላቸው፣ ስለ እግዚአብሔር እንዲያውቁ ሳይሆን እግዚአብሔርን ራሱን በማወቅ እንዲያድጉ ነው። ሰው እግዚአብሔርን እያወቀው ሲሄድ ሕይወቱ እየተለወጠና እግዚአብሔርን እየመሰለ ይሄዳል። እግዚአብሔን ማወቅ ለአማኝ እንደ ምግብ ነው።

"ጸሐይና ዝናብ ለአትክልት እድገት እንደሚሆኑት ፣ እግዚአብሔርን ማወቅም ለመንፈሳዊ ሕይወት ማደግና መብሰል የሚጠቅም ነው።"[8] ሰው እግዚአብሔርን እያወቀው የሚሄደው በስማ በለው (በኢንፎርሜሽን) ሳይሆን ከእርሱ ጋር ሕብረት በማድረግና ጊዜ በማሳለፍ ነው። ይህ አይነቱ ሕብረት ደግሞ ሲገኝ አማኝ ከላይ የተጠቀሰውን በጎ ሥራ ሁሉ ማፍራት ይችላል።

ሦስተኛው <u>**እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እንዲበረቱ ነው።**</u> ክርስቲያን በዚህ ዓለም እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘ ለጌታ እንደሚገባ ለመኖር እንዲችል ጉልበት ያስፈልገዋል። የዓለም፣ የሥጋና የሰይጣን ፈተና ቀላል እንዳልሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው። እነዚህ ሦስቱም ጥረታችው ከእግዚአብሔር መንገድ ሊያወጡን እንጂ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርቡን የሚመጡ ፈተናዎች አይደሉም። አማኝ ጉልበት ከሌለው በየመንገዱ እየተሰናከለ፣ ጌታን እያሳዘነ የሚመላለስ ከመሆኑ ሌላ ሕይወቱ ሁሌም የንስሐ ይሆናል።

በዚህ ክፍል የመጨረሻው የተጠቀሰው ነጥብ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። እግዚአብሔን አማኝ እንዲያመሰግን ሊያደርጉት የሚገቡት እልፍ ነገሮች አሉ። ጳውሎስ ግን እዚህ ጋር የቆላስይስ አማኞች እንዲያመሰግኑ የሚያደርጋቸውን አንድ ነጥብ ይጠቅሳል - "**በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን አብን እያመሰገናችሁ።**" እዚህ ጋር ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ብቃት ነው። አማኞቹ በራሳቸው ችሎታ በቅዱሳን ርስት ለመካፈል አልበቁም፣ **"ያበቃንን አብን"**፡የሚለው አባባል ብቃታቸው ከእግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል። እግዚአብሔር አማኞቹን ብቁ ያደረጋቸው አንድ ቤተ መንግስት እንዲገቡ አይደለም። ይህ አይነቱ ነገር በሰው የሚቻል ነው። እግዚአብሔር ግን ያበቃቸው ለቅዱሳን ርስት ነው። ይህ ርስት የማይጠፋ፣ እድፈት የሌለበት የማያልፍ ርስት ነው (1ኛ ጴጥ 1:3-5)። ይህንን በሰው የማይገኝ ብቃት ያገኘ አማኝ በእርግጥ እግዚአብሔን እንዲያመሰግን ይገባል።

**ከቁ 13-14** ባለው ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር እንዴት አማኞችን ለቅዱሳን ርስት ብቁ እንዳደረጋቸው ሦስት ነገሮችን ይገልጻል። **በመጀመሪያ** "**እርሱ ከጨለማ ስልጣን አዳነን**" ይላል። የጨለማ ስልጣን የሚባለው የሰይጣን

[8] Curtis Vaughan, *Colossians and Philemon* (Grand Rapids, 1980), p 31.

አገዛዝ ነው። ሰው ሁሉ ከፍጥረቱ በኃጢአትና በሰይጣን ስልጣን ስር ወድቆ ያለ መሆኑ ግልጽ ነው (ኤፌ 2:1-3)። አሁን ግን አማኞችን እግዚአብሔር ከዚያ ስልጣን ነጻ አውጥቷቸዋል። **ሁለተኛ** "**የኃጢአትን ስርየት**" አገኘን ይላል። በኃጢአት ለጠፋ ሰው ከኃጢአት ነጻ የሚወጣበትን መንገድ ያዘጋጀውና ክርስቶስን የላከው እግዚአብሔር ነው። ከጨለማው ስልጣን አውጥቶ ለቅዱሳን ርስት ለማብቃት በመጀመሪያ እግዚአብሔር በኃጢአት ስርየት ኃጢአተኛውን ቅዱስ ሊያደርገው አስፈልጎታል። ሦስተኛ "**ወደ ፍቅሩ ልጅ መንግስት አልፈለሰን**"። ይህ ፍልሰት የሚከናወነው ሰው ጌታን በሚያገኝበት ቅጽበት ነው። ሰው ክርስቶስን በሚቀበልበት ደቂቃ፣ ከሰይጣን መንግስት ነጻ ወጥቶ የክርስቶስ መንግስት ዜጋ ይሆናል። ይህ ዜጋ ደግሞ ወደፊት በመጨረሻ ዘመን የሚገለጥ የቅዱሳን ርስት በሰማይ ቀርቶለታል (1ኛ ጴጥ 3-5)። ስለዚህም ደግሞ አማኝ ለዚህ ድንቅ የ'እግዚአብሔር ስጦታ እግዚአብሔርን ቀንና ሌሊት ሊያመሰግን ይገባል። ይህ ዓይነት ሕይወት ለጌታ የሚገባ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ፡ነው።

***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. በቆላ. 1:9 ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ አማኞች ስለሚጸልይላቸው ነገሮች ተወያዩ? (የጸሎቱ ፍሬ አሳቦች ምንድ ናቸው?)
2. ሐዋርያው ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዲያውቁና ለጌታ በሚገባ ሕይወት እንዲመላለሱ" የሚጸልየው ለምድን ነው?
3. **በቆላ. 1:10-12** መሰረት በሕይወታችን **የእግዚአብሔርን ፈቃድ** ስናውቅ የሚከናወነው ለውጥ ምንድን ነው (አዲሱን መደበኛ ትርጉም ብናነብ የተሻለ እንረዳለን)?
4. **ቆላ. 1:13-14** ስናነብ እግዚአብሔር አምላካችን በሕይወታችን ውስጥ ያከናወናቸው ነገሮች ምንድ ናቸው ነው? ይህስ ሐዋርያው ጸሎት ጋር ምን ይገናኛል?
5. ከላይ የተጠቀሰው የሐዋርያው ጸሎት በዮሐንስ 17 ላይ ከተጠቀሰው ከክርስቶስ ጸሎት ጋር ምን ተመሳሳይነት እና ልዩነት አለው?

6. በዚህ ጥናት መሠረት የጸሎቶቻችን ርዕሶች በምድራዊ ነገሮች ላይ **ብቻ** ያተኮሩ እንዳይሆኑ ምን ተማርን?
7. እስካሁን ያየነውን በሉቃስ 11፡1-4፣ ከተጠቀሰው የ"አባታችን ሆይ" ጸሎት ጋር በማነጻጸር ስለ ጸሎት ሚዛናዊነት አብራሩ?
8. ከዛሬው ውይይት ባጠቃላይ ስለ ጸሎት የተማርነውን እናካፍላለን።

***መደምደሚያ፡-***

በመግቢያው ላይ እንዳየነው በዚህ ምድር ትልቁ ጥማትችን ሊሆን የሚገባው በምድራዊ ነገር ብቻ እንድንሞላ ሳይሆን፣ **እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ጌታን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት ለጌታ እንደሚገባ መኖር** ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ ላሉት አማኞች ከምንም ነገር ይልቅ ይህንን የሚጸልይላቸው። እኛም ለራሳችንም ሆነ ለሌላው ወገናችን የሚኖረን መሻት እንደዚህ ሊሆን ይገባል።

## ጥናት ስድስት
## የክርስቶስ ታላቅነትና ተግባሩ
## የንባብ ክፍል፦ ቆላ 1:15-23

**ዓላማ**

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑንና መዳንም (ድነት) የሚገኘው በእርሱ ብቻ መሆኑን ማስገንዘብ።

**መግቢያ**

የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትና ግብር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠ ቢሆንም ጌታ በምድር ይመላለስበት ከነበረበት ጊዜ አንስቶ እስከዛሬም ድረስ ስለማንነቱ ብዙ የተምታታ ነገሮች ይባላሉ። ጌታ ራሱ **"ሰዎች እኔ ማን እንደሆንኩ ይላሉ"** ብሎ በጠየቀ ጊዜ ሰዎች ስለማንነቱ ብዙ መላ ምቶች ያቀርቡ እንደነበር ተጽፏል (ማቴ 16:13-14)። በቆላስይስ ከተማም ስለ ክርስቶስ ማንነት ብዙ ግራ የሆኑ ትምህርቶች እንደሰጠ ግልጽ ነው። በተለይ በጥናታችን መግቢያ እንዳየነው ኖስቲሳዊያን (Gnostists) የክርስቶስን ማንነት የሚክድ አስተምህሮ ይሰጣሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ግን **በቆላ 1:15-23** ባለው ክፍል ስለ ክርስቶስ ማንነትና ሥራ ግራ የማያጋባና ጥርት ያለ ትምህርት ይሰጣል። በዚህም ትምህርቱ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና በሁሉ ነገር ላይ የበላይ መሆኑን እንዲሁም እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ከራሱ ጋር ሊያስታርቅ የወደደው ፍጹም መለኮት በሆነው በዚሁ በክርስቶስ መሆኑን አበክሮ ያስተምራል።

**እኛም በዚህ ክፍል በመመርኮዝ ዛሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነና ድነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ለምን እንደሆነ እናያለን። ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አንብበን መጥተን ከሆነ .... ወደ ውይይት ጥያቄዎች መሄድ እንችላለን።**

***<u>ትንታኔ/ማብራሪያ</u>***

ባለፈው ጥናት መጨረሻ ላይ እንዳየነው ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር አማኞችን ከጨለማ ስልጣን አድኖ ወደ ውድ ልጁ መንግስት እንዳፈለሳቸው ጽፎ

ነበረ ያቆመው **(ቆላ 1:13-14)**። ሆኖም ይህ የፍቅሩ ልጅ (ውድ ልጁ) ማን ነው ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል። ቀጥሎ ባለው ክፍል ማለትም ከቁ **15-20** ባለው ክፍል ሐዋርያው የክርስቶስን ማንነትና ታላቅነት ይዘረዝራል። ቀጥሎም ከቁ 21-23 ባለው ክፍል በክርስቶስ በማንነቱ ምክንያት የሠራውን ሥራ ይገልጻል።

የክርስቶስን ማንነት በሚገልጽበት ክፍል (ቁ 15-20)፣ ክርስቶስ በሁሉ የበላይ መሆኑን በሶስት ነጥቦች ያስረዳል። **1) ኢየሱስ ክርስቶስ መለኮት ነው (ቁ. 15) 2) ኢየሱስ ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ ጀማሪና ደጋፊ በመሆኑ ከፍጥረት ሁሉ በላይ ነው (ቁ 16-17) 3) ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን ራስ በመሆኑ ከቤተክርስቲያንም የበላይ ነው (ቁ 18)።**

የክርስቶስን መለኮትነት በሚያሰምርበት በመጀመሪያው ክፍል "**እርሱም የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤**" ይለናል። እዚህ ላይ **"ምሳሌ"** የሚለው ቃል ለአማርኛ አንባቢ ትንሽ ግር የሚያሰኝ ሊሆን ይችላል ምክንያቱም የአንድ ነገር ምሳሌ ከእውነተኛ ነገር ያነሰ ስለሚሆን ነው። ሆኖም ግን ጳውሎስ በዚህ ክፍል ለማሳየት የፈለገው ኢየሱስ ክርስቶስ በሁሉም ነገር ፍጹም አምላክ የሆነ ተምሳሌት መሆኑን ነው። ለምሳሌ ሁለት አንድ አንድ ሳንቲሞችን ብንወስድ አንደኛው ሳንቲም ለሌላኛው ፍጹም ምሳሌ ነው። እዚህ ጋር ግን ኢየሱስን "የማይታይ አምላክ ምሳሌ" ብሎ ነው የሚጠራው፤ ይህም በአንድ በኩል እግዚአብሔር አንድም መንፈስ በመሆኑ ብሎም ደግሞ ማንም ቀርቦ ሊመለከተው በማይችል ብርሃንና ክብር የሚኖር በመሆኑ እግዚአብሔር እንደማይታይ ሲያስገነዝበን (ዮሐ 1:18)፣ ክርስቶስ ግን አምላክ ሆኖ ሳለ በሚታይ የሰው ሥጋ ስለመጣ እግዚአብሔር በባሕርዩ ምን እንደሚመስል አሳየን (ዮሐ 1:18)። ስለዚህም ነው ጌታ **'እኔን ያየ አብን አይቷል"** (ዮሐ 14:9) ማለት የቻለው። የክርስቶስ ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ መምጣት ብዙዎች ማንነቱን እንዲሲቱ አድርጓቸዋል። በሥጋ ሲያዩት ሰው ብቻ መስሏቸው ንቀውታል፣ ተፍተውበታል፣ ሰድበውታል፣ ገርፈውታል በሎም ግድለውታል።

እውነታው ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ብቻ ሳይሆን **"የማይታይ አምላክ ምሳሌ"** ወይንም የዕብራዊያን ጸሐፊ እንዳስቀመጠው "እርሱ የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ" ነው (ዕብ 1:3)። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ በመሆኑ፣ የክርስቶስን ባህሪይ አይቶ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማየት ይችላል።

በመቀጠል ክርስቶስ ኢየሱስ ከፍጥረት ሁሉ በላይ መሆኑን "**ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው**" በማለት ያስገነዝባል። እዚህ ጋር በኩር የሚለው ቃል ለብዙዎች ግራ የሚያጋባ ነው ምክንያቱም በተለምዶ በኩር ማለት የመጀመሪያ ማለት ነው ልክ የበኩር ልጅ እንደምንለው። በዚህ ትርጓሜ መሰረት ይህ አረፍተ ነገር ክርስቶስ የመጀመሪያ ተፈጣሪ ነው ወደሚል አሳብ ሊወስደን ይችላል። ሆኖም ግን ጳውሎስ እዚህ ላይ እያለ ያለው በፍጹም ይህን ሀሳብ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ጳውሎስ ኢየሱስ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ያለው መጀመሪያ ስለተፈጠረ ሳይሆን የሁሉ ነገር ፈጣሪ ስለሆነ ነው፤ "**በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው**" እዚህ ጋር "**ተፈጥረዋልና"** ሲል ና የምትለዋ ፊደል ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በኩር ተብሎ እንደተጠራ ያመለክታል። በሌላ አባባል እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው ምክንያቱም በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና ማለት ይሆናል። በኩርነቱ፣ እርሱ ከፍጥረት መካከል መጀመሪያ ስለተፈጠረ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ በእርሱ አማካኝነት ስለፈጠረው ነው።[9]

ከዚህ ባሻገር "በኩር" ተብሎ **የተተረጎመው ቃል እንደ አገባቡ በጊዜ *ቀዳሚነትን* በደረጃ ደግሞ *የበላይነትን* ሊያመለክት ይችላል።**[10] በዚህ ክፍል ግን ሁለቱንም ሳያመለክት አይቀርም። ከጊዜ አንጻር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በኩር ነው ምክንያቱም ክፍሉ እንደሚለው "ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው"። እዚህ ጋር ልብ ልንለው የሚገባን ከፍጥረቱ መካከል የመጀመሪያው (በኩር) ነው አይደለም የሚለው፤ ነገር **ግን ከፍጥረት ሁሉ *በፊት* በኩር ነው።** በሌላ አባባል ፍጥረት ሁሉ ሳይኖር በፊት ነበረ ማለት ነው።

---

[9] N.T. Wright, *Colossians and Philemon* (Grand Rapids, 1989), P 71.
[10] Curtis Vaughan, *Colossians and Philemon* (Grand Rapids, 1980), p 38.

ከደረጃ አንጻር ደግሞ እርሱ ከፍጥረት ሁሉ በላይ ነው ምክንያቱም እርሱ (ክርስቶስ ኢየሱስ) ተፈጣሪ ሳይሆን ፈጣሪ ነው። ፈጣሪ ከፍጥረቱ እንደሚበልጥና የበለጠ ክብር እንደሚገባው እንዲሁ ክርስቶስም ነው። እዚህ ጋር በፍጥረቱና በክርስቶስ መካከል ያለውን ግንኙነት የገለጸበትን ሶስት አሳቦች ልብ ማለት ተገቢ ነው። **በመጀመሪያ** ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል። ይህ ሲባል ከፍጥረቱ ምንም የሚቀር ነገር የለም። "**የሚታዩት እና የማይታዩት ዙፋናት ቢሆኑ፣ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ስልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና** ..." (1:15-16)። **ሁለተኛ** "**ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል**"። ፍጥረት በክርስቶስ መፈጠር ብቻ ሳይሆን፣ የተፈጠሩት ለእርሱ ክብር ነው። የፍጥረት የመገኘቱ አላማና ፍጻሜ ለክርስቶስ ኢየሱስ ክብር ማምጣት ነው። **በሦስተኛ ደረጃ** ሁሉም "**በእርሱ ተጋጥሞአል።**" በሌላ አባባል ፍጥረት ተያይዞና ሥርዓት ይዞ ያለው በክርስቶስ ኢየሱስ ምክንያት ነው። ምድር በጸሐይ ዙሪያ ሥርዓትዋን ጠብቃ የምትሄደው፣ ወቅቶች ጊዜአቸውን ጠብቀው የሚለዋወጡት፣ ጠፈራት ምህዋራቸውን ጠብቀው የሚዞሩት፣ በሳይንስ ሕግ ብቻ ሳይሆን **በክርስቶስ ምክንያት** ነው።[11] ያለ ክርስቶስ ፍጥረት መኖር አይችልም። ስለዚህም በእርግጥ ክርስቶስ የፍጥረት ሁሉ ራስ ወይንም በኩር ነው።

ክርስቶስ ኢየሱስ ከፍጥረቱ ሁሉ በላይ እንደሆነ ካመለከተ በኋላ፣ ከቤተክርስቲያንም በላይ እንደሆነ ያስተምራል። "**እርሱም የአካሉ ማለት የቤተክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።**" ቤተክርስቲያን የአማኞች ወይንም በክርስቶስ አምነው አዲስ ፍጥረት የሆኑ ሰዎች ሕብረት ነው። እዚህ ጋር ጳውሎስ የፍጥረት ብቻ ሳይሆን የአዲስ ፍጥረት (የቤተክርስቲያንም) ራስ ነው ይለናል። ራስ መሆን ብቻ ሳይሆን እሱ የቤተክርስቲያን መጀመሪያ፣ ከሙታንም በኩር ነው። እዚህ ጋር መጀመሪያ የሚለው ቃል መነሻ የሚለውን አሳብ የሚያመለክት ሲሆን፣ የቤተክርስቲያን መነሻ ምንጭና ምክንያት ክርስቶስ መሆኑን ያመለክታል። ከሙታን በኩር የሚለው አሳብ ክርስቶስ ኢየሱስ እውነተኛውን ትንሳኤ

[11] William Barclay, *THE LETTERS TO THE PHILLIPIANS, COLOSSIANS AND THESSALONIANS* (Philadelphia, 1975), 120.

በማግኘት ቀዳሚ መሆኑን ይጠቁማል። የዚህ ሁሉ አላማ ግን ክርስቶስ ኢየሱስ "**በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ**" ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ ኢየሱስ በሁሉ የበላይ መሆኑን በአጽንኦት ካስረዳ በኋላ ሁለት አሳቦችን በሚቀጥሉት ቁጥሮች ያስረዳል። ክርስቶስ በሁሉ የበላይ እንዲሆን የሆነበትን ሁለት ምክንያቶች ያስቀምጣል። **አንደኛ** እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በክርስቶስ እንዲኖር ወዷል (1:19)፤ **ሁለተኛ** ፍጥረትን ሁሉ በሞቱ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያስታርቅ እግዚአብሔር ወዷል (1:20-23)።

"**እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር**" ፈቅዷል ሲባል ሙላቱ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ምንድነው የሚል ጥያቄ ማንሳቱ የማይቀር ነው። ብዙ የተለያዩ መልሶች ቢሰጡም ግን ይህ ነገር የሚያመለክተው ሙሉ መለኮትነትን ወይንም የእግዚአብሔርን ሙሉ ማንነት የሚያመለክት ነው የሚለው አሳብ አሳማኝ ነው። በሌላ አባባል ኢየሱስ ፍጹም መለኮት፣ ፍጹም አምላክ ነው።

ከዚህም ባሻገር እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል "**በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይንም በሰማይ ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአል**"። እዚህ ጋር በምድር ወይንም በሰማይ ያሉትን እንዲያስታርቅ ሲል ምን ለማለት እደፈለገ ለመረዳት ለብዙዎች ያስቸግራል። በተለይም በሰማይ ያሉትን ሲል ምን ማለቱ ነው የሚለው ጥያቄ ለብዙዎች አወዛጋቢ ነው። ሆኖም ግን እዚህ ጋር እግዚአብሔር በክርስቶስ አጠቃላይ ፍጥረት ከእርሱ ጋር እንዲያስታርቅና ሰላምን እንዲያወርድ መውደዱን የሚያመለክት ነው። ኃጢአት ወደ አለም በገባ ጊዜ ሰላም የጠፋው በሰው ልጅ መካከል ብቻ ሳይሆን በፍጥረትም ውስጥ ጭምር ነው። በእርግማን ስር የወደቀው መላው ፍጥረት ነው። ስለዚህም ነው በሮሜ 8 ላይ ፍጥረት ሁሉ የፍጻሜን ቀን እንደሚጠብቅ የሚነግረን። ይህ ሲባል ግን በክርስቶስ ያለመነ ሁሉ በዚህ ጥቅስ መሰረት ድነትን ያገኛል ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። በእርግጥም ዝቅ ብለን ስናነብ በእርግጥ ይህን ድነት የሚገኘው በወንጌል በማመንና በመጽናት መሆኑን ይነግረናል።

በቁ. 23 ላይ ይህ ድነት (እርቅ) እውነተኛ መሆኑ የሚለካበትን መንገድ ይገልጻል፡፡ "**ይህም ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ ከሰማችሁትም ወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል፤**" በማለት የዳነውና እርቅን በክርስቶስ በማመን የተቀበለው ሰው እስከመጨረሻው እንደሚጸና ያመለክተናል፡፡

***<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>***

1. ቆላ 1፡ 15-18 ባለው ክፍል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚነግረን ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በቆላ. 1:15-16 ላይ "**... የማይታይ አምላክ ምሳሌ** [ተምሳሌት] ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው? ዕብ 1:3 እና 1 ጢሞ 1:17ን እነዚህ ሁለት ክፍሎች ይነበቡ፡፡
3. ቆላ 1፡17-20 መሠረት በክርስቶስ ኢየሱስ ካልሆነ በስተቀር ሰው ድነትን (ከእግዚአብሔር ጋር እርቅን) በሌላ በምንም መንገድ ማግኘት የማይችለው ለምድን ነው (ሐዋ ሥራ 4:12)?
4. ቆላ 1፡21-22 በማንበብ ከላይ ካሉት ቁጥሮች ሀሳብ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ ተወያዩ፡፡
5. በቆላ 1:22 መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀበት ዋና ዓላማ ምንድ ነው?
6. ከላይ ባየነው መሠረት ማለትም **<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ ሆኖ ሳለ</u>** በቆላ 1:22 ላይ " ... በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ (አዲሱ መደበኛ ትርጉም)" የሚለውን ሀሳብ ከፊልጵ 2:5-8 በማንበብ ተወያዩ?
7. ከዛሬው ጥናት ስለ ክርስቶስ የተማርከውን ሶስት ነገሮች የተማራችሁትን አስረዱ፡፡
8. ዛሬ በጸሎታችን ጌታችን ኢየሱስ ለድነታችን ስለ ከፈለው ዋጋ በማሰብ እናመስግን

***መደምደሚያ***

እንዲህ ከላይ እንዳየነው ቆላ 1:15-23 ያለው ክፍል፣ የክርስቶስን ማንነትና ሥራ አጠርና ጠንከር ባለ መልኩ ይገልጻል። በዚህም 1ኛ) ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን፣ 2ኛ) ለፍጥረትና ለቤተክርስቲያን መገኘት ምክንያትና የበላይ መሆኑን 3ኛ) እግዚአብሔርም ሙላቱ እንዲኖርበትና አለማትንና ፍጥረታትን ከእርሱ ጋር እንዲያስታርቅ የፈቀደው በዚሁ በክርስቶስ እንደሆነ አይተናል። ክርስቶስ ኢየሱስም በመሰቀልና ደሙን በማፍሰስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚያምኑበትን ከእግዚአብሔር ያስታርቃል። ስለዚህም ድነት ያለ ክርስቶስ ፈጽሞ ሊገኝ አይችልም። ወንጌልም የሚያስተምረው እውነት ይህንኑ ነው።

## ጥናት ሰባት
## የሐዋርያው ጳውሎስ ታላቅ የአገልግሎት ሸክም
## የንባብ ክፍል፦ ቆላ 1:24 – 2:5

**ዓላማ**

እውነተኛ አገልግሎት ብዙ ዋጋ እንደሚያስከፍል በመረዳት በሙሉ መስጠት እንድናገለግል ማስገንዘብ

**መግቢያ**

ጌታንና ሕዝቡን የማገልገል ፍላጎት በብዙዎች ልብ ውስጥ የሚቀጣጠል፣ በአገልግሎት የተሰማሩትም ሰዎች ከብዙ ደስታ ጋር የሚያደርጉት ነገር ነው። ነገር ግን በአገልግሎት መሰማራት ከውጭ እንደሚመስለው ቀላል ነገር አይደለም። ብዙ ፈታኝ የሆኑ ነገሮችን ማለፍ፣ መከራን መቀበል እንዲሁም መሰጠትን ይጠይቃል (**2ቆሮ.11:11-28**)።

የሐዋርያው ጳውሎስን አገልግሎት በዚህ ክፍል ውስጥም ስንመለከት፣ አገልግሎቱን የሚያደርገው ከደስታ ጋር ነው። ነገር ግን አገልግሎቱ ቀላል ዋጋ የሚጠይቅ ሆኖ አይደለም። በአገልግሎቱ ምክንያት በእስር ላይ ሆኖ መከራን እየተቀበለ ባለበት ሰዓት ነው ይህንን መልዕክት የጻፈው። ሆኖም ወህኒ መጣሉ ለአገልግሎት ያለውን ተሰጥኦ አልቀነሰውም፣ በእስር ላይም ሆኖ ግን በመልዕክቶቹ ቤተ ክርስቲያናትን ይመክራል፣ ስለአብያተ ክርስቲያናትና ስለምዕመናን ይጸልያል፣ እውነተኛውን ክርስቶስን ለመስበክ ይደክማል፣ ሰዎችን ፍጹም ለማድረግ ይጥራል። እንዲሁም አማኞች በሐሰት ትምህርት እንዳይወሰዱ በጸሎትና አቅሙ በሚፈቅደው ሁሉ በጹሐፍ ይጋደላል።

በእኛም ሕይወት አገልግሎት እንዲሁ ሊሆን ይገባል። ጌታን የማገልግለ ፍላጎት ያለው መሆን መልካም ነው። ጌታን ማገልገል የሚፈልግ መልካምን ይመኛል። ሆኖም ግን ፍሬያማና ጌታን ደስ የሚያሰኝ፣ ለኛም የሚያረካ አገልግሎት እንዲኖረን የሚጠይቀውን ዋጋና መስዋዕትነት ለመክፈል፣ ለምናገለግላቸውም ፈጽሞ ለመሰጠት ፈቃደኞችና ቆራጦች እንድንሆን ይገባል

(ሉቃ 9:23)። በዛሬው ጥናታችንም ከጳውሎስ አገልግሎት በመነሳት ይህንን እውነት እንማራለን።

***ትንታኔ/ማብራሪያ***

**በቁ. 24** "**አሁን በመከራዬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል**" ይላል። ክፍሉ ሲጀመር "**አሁን**" በማለት ነው። ይህ ቃል ሁለት ዓይነት ትርጉም ሊሰጥ ይችላል። በአንድ በኩል ስለዚህ ማለት ሊሆን ይችላል። በዚያ መልኩ ከወሰድነው ከላይ የተጻፈውን እውነት ቀጥሎ ከሚጽፈው አሳብ ጋር የሚያያይዝ ቃል ነው ማለት ነው። ባለፈው እንዳየነው ከላይ የነበረው ክፍል ክርስቶስ አምላክ መሆኑንና እርሱ ከፍጥረትም ሆነ ከቤተክርስቲያን በላይ መሆኑን፣ ደግሞም እግዚአብሔር ዓለሙን ከራሱ ጋር በክርስቶስ ለማስታረቅ ወዶ መፈጸሙን አሳይቷል። ጳውሎስም ይህንን ወንጌል ለመስበክ አገልጋይ ሆኗል። ስለዚህ (ይህንን ታላቅ ወንጌል ለመስበክ ስለተጥራሁ ሐዋ 9:15-16) ስለ እናንተ በምቀበለው መከራም ውስጥ እንኳ ደስ ይለኛል ማለቱ ይሆናል። በሌላ በኩል አሁን የሚለው ቃል ጊዜን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመከራ ደስ ይለኛል ከማለት አልፎ ግን ለብዙዎች ግራ የሚያጋባ ነገር ይጽፋል። "**ስለ አካሉም ማለት ስለ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ**" የሚለው ቃል በእርግጥም አወዛጋቢ ነው። በመጀመሪያ ስለ ቤተክርስቲያን በተቀበለው መከራ ውስጥ የጎደለ ነገር አለ? በሁለተኛ ደረጃ እንዴትስ ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ወይም ሌላ ማንም ሰው በክርስቶስ መከራ የጎደለውን የሚሞላው የሚሉት ጥያቄዎች መልስ የሚያስፈልጋቸው ናቸው።

ምንም እንኳን ነገሩ ጥያቄ ቢፈጥርም መልሱ ግን ቀላል ነው። በመጀመሪያ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከተቀበለው መከራ የጎደለና ሌላ ሊሞላለት የሚያፈልገው ነገር አይደለም። ሆኖም ግን ክርስቲያኖች የሚቀበሉት መከራ የክርስቶስ መከራ ነው። ክርስቶስ ራስ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካል እንደመሆኗ፣ አማኞች መከራ ሲቀበሉ፣ ክርስቲያኖች ሲሰደዱ፣ ክርስቶስ መከራ እንደተቀበለና እንደተሰደደ ነው

የሚቆጠረው። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ጌታ ከመምጣቱ በፊት ክርስቲያኖችን ያሳድድና ያሳስር ነበር። ጌታ በተገናኘው ጊዜ ግን ጌታ ያለው የምታሳድደው እኔ ነው ነበር ያለው (ሐዋ 9:5)። በዚህም መሰረት፣ ለሰው ልጅ ኃጢአት የተቀበለው የመስቀል መከራ ፍጹምና ምንም የማይወጣለት ቢሆንም፣ ግን አካሉ (ቤተ ክርስቲያን) በዚህ ምድር ላይ የምታልፍበት መከራ ግን ገና አልተጠናቀቀም። ቤተክርስቲያን ገና ጌታ እስከሚመጣ በተለያዩ መከራዎች ውስጥ ታልፋለች። አገልጋዮች መከራን ሲቀበሉ እየተቀበሉ ያሉት የክርስቶስን መከራ ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ ስለ ቤተክርስቲያን ከተቀበለው መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ የሚለው። ይህ ለሐዋርያው ጳውሎስ ብቻም ሳይሆን ዛሬም አማኞች በጌታ ምክንያት መከራን ሲቀበሉ አብሮ መከራ የሚቀበለው ክርስቶስም ነው … የሱ አካል ስለሆኑ። አማኞች መከራን ሲቀበሉ የክርስቶስን መከራ እየፈጸሙ ነው።

ከቁ 25-27 ባለው የእግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ መጥራቱንና ያም ቃል ምስጢር እንደነበረ ያሳያል። “**ስለ እናንተ እንደተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፣ የ’እግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንኩ**” ይላል። እዚህ ጋ “መጋቢነት” የሚለው ቃል ሃላፊነት ወይንም ባለአደራነት ለማለት ነው። ይህም ባለ አደራነት የተሰጠኝ “ስለ እናንተ” ወይንም ለእናንተ ጥቅም ነው ይላል። በሌላ አባባል ሐዋርያው ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰብክ የተጠራው ለቆላስይስ ሰዎችና ለሌሎችም አህዛብ ጥቅም ነው። ግን እዚህ ጋ ምንድን ነው ይህ እንዲሰብክ የተጠራው የእግዚአብሔር ቃል የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሐዋርያው ጳውሎስ ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች ውስጥ ለዚህ መልስ ይሰጣል። “**ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምስጢር ነው፣ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል፤**” ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲሰብክ የተጠራው የእግዚአብሔር ቃል በዘመናት ሁሉ እንደገናም በትውልዶች ሁሉ ውስጥ ያልታወቀና ያልታሰበ ነገር ነበር። ይህ እግዚአብሔር ምስጢር ያደረገው አሁን ግን ለሰዎች የገለጠው እውነት “**የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ (በአሕዛብ) ዘንድ መሆኑ ነው።**” ድሮ ድሮ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚባሉት

አይሁዳዊያን ብቻ ነበሩ። ተስፋ ያላቸው እነሱ እንደሆኑ ነበረ የሚታሰበው፣ አሁን ግን እግዚአብሔር አይሁዳዊያንን ብቻ ሳይሆን በልጁ የሚያምኑትን አሕዛብንም ጭምር ወደራሱ አቅርቦ ክርስቶስ በመካከላቸው አለ። ይህ እውነት በፊት ምጢር ነበር አሁን ግን በክርስቶስ ተገልጧል (ኤፌ 3:3-6 ያለውን ያወዳድሩ)። ባጭሩ ሐዋርያው ጳውሎስ  የተጠራው ወንጌልን እንዲሰብክ ነው። ወንጌል ደግሞ አይሁድ አሕዛብ አይልም በክርስቶስ የሚያምነው ማንም ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋ ወራሽ ነው።

ከቁ 28-29 ሐዋርያው ጳውሎስ ለዚህ ጥሪ ታማኝ መሆኑንና ለዚህ እንደሚተጋ ይናገራል። ለአንድ አላማ መጠራት አንድ ነገር ነው፣ ለተጠሩት ጥሪ ታማኝ መሆን ሌላ ነገር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የተጠራው ክርስቶስን እንዲሰብክ ነው፣ እሱም በአገልግሎቱ በታማኝነት የሚያደርገው ክርስቶስን መስበክ ነው። "**እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሰጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው፤**" ይላል። ሰዎች ክርስቶስን እንዲሰብኩ ተጠርተው በአገልግሎታቸው ግን የሚሰሩት ሌላ ሲሆን ግር ይላል፣ በሐዋርያው ጳውሎስ ዘንድ ግን ጥሪው ክርስቶስን መስበክ ነው፣ ሥራውም እሱ ነው። እዚህ ጋር ግን ሶስት ነገሮች ልብ እንድንል ይገባል። የመጀመሪያው የስብከቱ፣ የትምህርቱና የተግሳጹ አላማ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሁሉ የምናደርገው ለአንድ አላማ እርሱም **በክርስቶስ ፍጹም የሆነ ሰውን እናቀርብ** ዘንድ ነው ይላል። ሁለተኛ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚጠቀምበት መንገድ ነው። ፍጹም የሆነ ሰውን ለማስገኘት እነ ሐዋርያው ጳውሎስ ሰውን ሁሉ ይገስጻሉ፣ የሚሰማውን ያስተምራሉ። ሦስተኛ ይህ ሁሉ የሚደረገው ያለ ልዩነት አሕዛብና አይሁድ ሳይባል ለሰው ሁሉ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ ሰዎችን እናስተምራለንና እንመክራለን ብቻ ብሎ አያቆምም "**ነገር ግን ለዚህም ነገር ደግሞ በእኔ በኃይል እንደሚሰራ እንደ አሠራሩ እየተጋደሁ እደክማለሁ።**" ይላል። እዚህ ጋ መጋደልና መድከም የሚሉትን ቃላት ልብ ይበሉ። መጋደል የሚለው ቃል ትግልን የሚያመለክት ቃል ነው ልክ በትግል ወይንም በቦክስ ግጥሚያ ቦታ ስፖርተኛ እንደሚታገለው። ድካም ጉልበት እስከማይኖረን ስንሰራ የሚገጥመንን የአካል መዛል ያመለክታል። አገልግሎት

ከባድ ሥራ (hard work) ነው። ይህንን ስናይ አገልግሎትን አጥብቀንና አክብረን ልንይዝ እንደሚገባ ያሳስበናል። ሐዋርያው ጳውሎስ ትጋቱና ጥንቃቄው ለሚሰብከው ቃልና ለሚሰሙትም ሰዎች ጭምር ነው።

በ2:1-5 ባለው ይህንኑ አሳብ ያንጸባርቃል። "**ስለ እናንተና በሎዶቅያ ስላሉት ፊቴንም በሥጋ ስላላዩት እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁና፤**" በማለት የ'እግዚአብሔርን ቃል ለመስበክ እንደሚጋደለው ሁሉ ደግሞ ስለ አማኞች እደሚጋደል ይናገራል። እዚህ ጋ መጋደል የሚለው ቃል ከላይ በ1:29 ላይ ካለው ቃል ጋር የሚዛመድ ሲሆን ስለነዚህ ሰዎች በጸሎት የሚጋደልላቸውን ተጋድሎ ሳያመለክት አይቀርም። በእስር ቤት እንደመሆኑ በአካል ተገኝቶ ከሃሰት አስተማሪዎች ጋር ፊት ለፊት ገጥሞ ሊጋደልላቸው ባይችልም፣ በጸሎቱና በመልዕክቱ ግን ይጋደልላቸዋል። አንደኛ ልባቸው እንዲጸና መጸለይና ሁለተኛ የእግዚአብሔር ምስጢር ክርስቶስ እንደሆነ እንዲያውቅ መጋደል። በኖስቲካዊያኑ ፍልስፍና ሳይሆን የእግዚአብሔር ጥበብና እውቀት ሁሉ የተሰወረው በክርስቶስ ውስጥ ነው። ሰው ክርስቶስን ሲያገኝ፣ ሌላ ምንም አያስፈልገውም በክርስቶስ ሁሉም ይኖረዋል። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል ያለውን ምክር ይለግሳል- "**ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህንን እላለሁ።**"

ክፍሉን ሲጨርስ ሐዋርያው ጳውሎስ እርካታው ወይንም ደስታው በአማኞች ሥርዓትና እምነት መጽናት መሆኑን በመናገር ነው። ይህንን ክፍል ሲጀምርም ለእነርሱ በሚቀበለው መከራ ደስተኛ እንደሆነ በመግለጽ እንደነበረ አይተናል። ባጭሩ ሐዋርያው ጳውሎስ ደስታው በአገልግሎቱ መሳካት፣ ሰዎች በጌታ ሲበረቱ ማየት ነው። ስለዚህ ምክንያት መከራን መቀበል አይከብደውም፣ ስለ አገልግሎቱ ሲል ቢሰብክ፣ ቢጋደል፣ ቢጸልይ ሰዎችን ቢመክርና ቢገስጽ ቅር አይለውም። ይልቅስ በመከራም እንኳን ጌታን ሲያገለግል ደስ ይለዋል።

**<u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>**

1. በቆላ 1፡24 ላይ "... በሥጋዬ በክርስቶስ መከራ የጎደለውን እፈጽማለሁ" ሲል ምን ማለቱ ነው (ሮሜ 8፡17፣2ጢሞ 1፡8)?
2. በቆላ.1፡24-25 ሐዋርያው ጳውሎስ የአገልግሎቱን ኃላፊነት በምን ዓይነት መንገድ እየፈጸመ እንደነበረ ተነጋገሩ? ከዚህስ ስለ አገልግሎት አደራ ምን ያስተምረናል (2 ጢሞ 4፡7-8) ?
3. በቆላ 1፡26-27 ሐዋርያው ጳውሎስ የሚናገረው ምስጢር ምንድን ነው? ይህ ምስጢር ለማን ተገለጠ ( ቆላ 2፡3)?
4. በቆላ 1:28-29 መሠረት የሐዋርያው የአገልግሎት ግብ ምንድ ነው? ከዚህ ምን እንማራለን?
5. ቆላ 2:1-2 ሐዋርያው ጳውሎስ በዓይኑ ላላያቸው ወገኖች በጸሎት የሚጋደለው ለምንድ ነው? ከዚህ ምን እንማራለን?
6. ቆላ 2:4ን ሲናነብ ምን ያመለክተናል? ይህስ ሀሳብ ከቆላስይስ መልዕክት ዋና ዓላማ ጋር እንዴት ይገናኛል? አብራሩ።
7. ከዛሬው ጥናት ስለ አገልግሎት አደራ እና ስለሚያስከፍለው ዋጋ ምን ተማራችሁ?

**መደምደሚያ**

አገልግሎት በሰዎች እጅ ያምራል። ብዙዎች እንደ እከሌ ብርቱ አገልጋይ ብሆን ብለው ይመኛሉ። ነገር ግን ይህ አገልግሎት ያለ ዋጋ፣ ያለ ድካም፣ ያለ ተጋድሎ አይመጣም። እግዚአብሔርም አገልግሎትን የሚባርከው ከልቡ ተሰጥቶ አገልግሎት ሕይወቴ ነው ብሎ ለያዘው ነው። ስለዚህም እኛም ልክ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ በእንደዚህ ዓይነት ተሰጥኦ እናገለግል ዘንድ እንድንችል እንቁረጥ፣ እንጸልይ እንዲሁም እንጋደል።

# ጥናት ስምንት
# ከሰው ሰራሽ ሥርዓትና ትምህርት በክርስቶስ ነጻ መሆን
# (ክርስቶስ ፍጹም ብቃታችን ነው)
# የንባብ ክፍል፡- ቆላ 2:6 -15

## ዓላማ

አማኞች በክርስቶስ ፍጹምና ሙሉ መሆናቸውን አውቀው በክርስቶስ እንዲበረቱና እንዲያድጉ ማሳሰብ

## መግቢያ

የዛሬውን ጥናት (ቆላ 2:6-15) የተመሠረት ሲሆን በቆላስይስ ከተማም በክርስቶስ ማመን ብቻ በቂ እንዳይደለና ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ሌሎች ልምምዶችን ማድረግ ተገቢ እንደሆነ የሚያስተምር ትምህርት እና ፍልስፍና ተነስቶ ነበረ። ሆኖም ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ሙሉ ብቃታቸው መሆኑን በማሳሰብ አማኞቹ ወደ ሀሰተኛ ትምህርት እና ፍልስፍና እንዳያዘነብሉ እና እንዳይማረኩ ነገር ግን በክርስቶስ እንዲጎለብቱ ያሳስባል **(ቆላ.2:6-8)።** በመቀጠል በጌታ መሆን በሥጋ መገረዝ እጅግ የላቀ እና በቂ ነው ይላል **(ቆላ.2፡ 9-11)፤ይህ ደግሞ የአይሁዶችን የህግ ትምህርት ያስተካክላል (የገላቲያ መልዕክት በጥሩ ሁኔታ ያስተምራል)፤በክርስቶስ ማመን በቂ ነው ። ቆላ.2:12-15** ደግሞ በክርስቶስ የተገኘውን ድል ያበስራል።

በእኛም ዘመን እንዲሁም ጎድለናል ብለን ካሰብን በማይሆን ትምህርት፣ አካሄድ የማይሆን ወጥመድ ውስጥ መግባታችን አይቀሬ ነው። ነገር ግን በክርስቶስ ሙሉ እንደሆንን አውቀን፣ አለ፣ ጎደለ በምንለውም በጌታ ረክተን እንድንኖር ይህ ክፍል ያሳስበናል።

**ትንታኔ (ማብራሪያ)**

በባለፈው የጥናታችን ምንባብ መጨረሻ ላይ ማለትም ቆላ 2:3-4 ባለው ሐዋርያው ጳውሎስ በክርስቶስ ኢየሱስ ውስጥ የጥበብ እና የእውቀት መዝገብ ሁሉ ስለተሰወረ፣ ከእርሱ ሌላ ማንንም እንዳይሹ እንዲሁም ማንም በሚያባብል ቃል ከዚህ እውነት እንዳይወስዳቸው አስጠንቅቆ ነበር። ይህ ጥናት ከዚህ አሳብ የሚንደረደር ነው። በጥናታችን መግቢያ ላይ እንዳየነው በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የሀሰት ትምህርቶች ተነስተው ነበረ። **<u>እነዚህም ትምህርቶች ለመዳን ክርስቶስ ብቻ እንደማይበቃ ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ሙላት ለመድረስ ሰው የተለያዩ ስራዓቶችን መጠበቅ እንዳለበት፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አሉ የሚባሉትን መላዕክት ማምለክ እንዳለበት፣ የተለያዩ እውቀት ጥበብ ማካበት እንዳለበት የሚያስተምሩ ነበሩ።</u>** በዚህ ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ የመልዕክቱን ዋና ነጥብ በማንሳት ክርስቶስ ኢየሱስ ለአማኞች በቂ እንደሆነ ያስተምራል። ስለዚህም ሰው መቆምና መጽናት ያለበት በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው።

ይህንን እውነት ለማስመር በመጀመሪያ **ከቁ 6-7** አማኞቹ በክርስቶስ እንዲተከሉና እንዲያድጉ ያሳስባል። **በቁ. 8** ላይ ከዚህ ከክርስቶስ ትምህርት ውጪ የሆነው አስተምህሮ የማይጠቅም ባዶ መሆኑን ያሳያል። **ከቁ.9-10** አማኞች ሙሉ በሆነው በክርስቶስ ሙሉ መሆናቸውን ያስጨብጣል። **ከቁ 11-15** ባለው እንዴት አማኞች በክርስቶስ ሙሉ እንደተደረጉ ያሳያል። በመጀመሪያ በክርስቶስ መንፈሳዊ መገረዝን መቀበላቸውን ያነሳል **(ቁ 11-12)**፣ ቀጥሎም በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር ሞተው በመነሳት የኃጢአት ይቅርታንና አዲስ ሕይወትን መቀበላቸውን ይዘግባል **(ቁ. 13**)፣ በስተመጨረሻም በክርስቶስ መስቀል አማኞቹ የሚከሰሱበት የዕዳ ጽህፈት መደምሰሱንና ክፉ መንፈሳዊያን ሰራዊቶችም (አለቅነትና ስልጣናት) በመስቀሉ ድል መነሳታቸውን ይገልጻል።

ክፍሉን ሲጀምር "**እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ፤ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፣ እንደተማራችሁትም**

**በኃይማኖት ጽኑ፣ ምሥጋናም ይብዛላችሁ**” ይላል። እዚህ ጋር “እንደተቀበላችሁት” የሚለው ቃል በአንዳንዶች ዘንድ ጌታ ኢየሱስን የግል አዳኝ አድርጎ መቀበልን የሚያመለክት እንደሆነ ቢያምኑም ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ አዋቂዎች ግን የተቀበላችሁትን የክርስቶስ ትምህርትና ባህል ለማለት እንደሆነ ያስተምራሉ።

በእርግጥም ዝቅ ብሎ “እንደ ተማራችሁትም በሃይማኖት ጽኑ” ስለሚል ይህ አሳብ የሚያስኬድ ይመስላል። ሆኖም ግን በየትኛውም መረዳት ብንወስደው የሐዋርያው ጳውሎስ ምክር አማኞቹ በጌታ እንዲድጉና እንዲጸኑ ነው።

እዚህ ጋር “**ተመላለሱ**”፣ “**ሥር ሰደዱ**”፣ “**ታነጹ**” **እና** “**ጽኑ**” የሚሉትን ቃላቶች ማስተዋል ይጠቅማል። አማኞቹ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል።

ነገር ግን ከዚያ በኋላ እንዴት ነው መኖር ያለባቸው ለሚለው እነዚህ ቃላቶች የሚያስጨብጡት እውነት አለ። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ “ተመላለሱ” የሚለው ቃል ክርስቲያናዊ አካሄድን ያመለክታል። <u>**ስለዚህም “በእርሱ (በክርስቶስ) ተመላለሱ” ሲባል እንደ ክርስቶስ ትምህርት፣ እሱን እንዳመነ ሰው ተመላለሱ የሚል ትርጉም ይሰጣል።**</u> በእርሱ “ሥር ሰዳችሁ፣ በእርሱ ታነጹ” የሚሉት ሁለት አሳቦች የተክልንና የህንጻን ምሳሌ የሚያመለክቱ ናቸው። አትክልት በንፋስ እንዳይወድቅ እንዲሁም ለአትክልቱ አስፈላጊ የሆነን ንጥረ ነገር ለማቅረብ በጥልቀት ሥር ሊሰድ ያፈልገዋል። እንዲሁ ክርስቲይኖች በሚመጣው የትምህርት ነፋስ ሁሉ እንዳይፍገመገሙ በክርስቶስ ትምህርት ሥር ሊሰዱ ይገባል። በሌላ በኩል ሕንጻ የሚታነጸው በመሰረት ላይ ነው። ሕንጻው በመሰረቱ ላይ እየታነጸ ነው ከጊዜ ወደ ጊዜ ወደ ፍጻሜ የሚደረሰው። ክርስቲያንም እንዲዚያው ነው። ሐዋርያው በክርስቶስ ሥር ሰደው እንዲታነጹ ወይም እንዲጎለብቱ ነው ጥሪው። ከዚህም በላይ በተማሩት የ’እምነት ትምህርት እንዲጸኑ ያሳስባል። ጽናት ባመኑበት ነገር መርጋትንና አለመወላወልን ያመላከታል። እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ወደ ታች ሥር መስደድን ወደ ላይ ደግሞ ማደግን (መታነጽን) ይጠይቃል። አሁን ጥሪው በዚሁ በጀመሩት በክርስቶስ እያደጉ፣ እየጨመሩ እንዲሄዱ እየጠነገሩ እየጸኑ እንዲሄዱ ነው።

**<u>እንግዲህ በክርስቶስ እንዲኀለብቱ ከመከረ በኋላ፣ በቁ. 8 ላይ ደግሞ በክርስቶስ ላይ እንዳይጸኑ ለሚያስተምር ትምህርት ጆሮ እንዳይሰጡ ያስጠነቅቃል።</u>** **"እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን እንደ ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት ባለ ፍልስፍና በከንቱ መታለል ማንም እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።"** እዚህ ጋ " እንዳይማርካችሁ" የሚለው ቃል ሊሰመርበት ይገባል። ምርኮ በጦርነት ጊዜ አንድ ወታደር ከሚደክምለት የጦር ክፍል በጠላት እጅ መግባትን ያሳያል። መማረክና መማ'ረክ የሚባል ነገር ካለ ጥልና ጦር መኖሩ ግልጽ ነው። እዚህም የሐዋርያው ጳውሎስ ምክር ለክርስቶስ ተቃራኒ እና ጠላት ለሆነ ትምህርት እጅ እንዳይሰጡ ነው። ለዚህም ሦስት ምክንያቶችን ይሰጣል። በመጀመሪያ እንደዚህ ያለው ትምህርት እንደ ክርስቶስ አይደለም። ወይንም ሰው በክርስቶስ ብቁ መሆኑንና በእርሱ ብቻ ሥር እንዲሰድ፣ በ'እርሱ ብቻ እንዲያድግና እንዲጸና አያስተምረም። እንዲያውም ሰው በክርስቶስ ብቻ ብቁ ስላይደለ፣ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ለመድረስ የመገረዝን ሥርዓት እንዲጠብቅ፣ ቀናትን እዲያከብረ፣ መላዕክትን እንዲያመልክና በብህትውና እንዲመላለስ የሚመክር ነው። ሁለተኛ ይህ አይነቱ ትምህርት፣ "እንደ ሰው ወግና እንደ አለማዊ እንደ መጀመሪያ ትምህርት" ዓይነት ነው። "የሰው ወግ" ልክ ፈሪሳዊያኖች ያደርጉ እንደነበረው ስለ ሰው ሥርዓት የእግዚአብሔርን ሕግ የሚያስጥል ነው (ማቴ 15:1-9)። ይህም በቆላስይስ የነበረው የሐሰት ትምህርት የ'እግዚአብሔርን እውነት ሳይሆን የሰውን ወግ የሚያስቀድም እንደነበረ ያሳያል። ይህም ብቻ ሳይሆን እንደ "አለማዊ እንደመጀመሪያ ትምህርት" ያለ ነው። በዚህ አባባል ላይ ብዙ ትንታኔ ቢሰጥም ግን ፍሬ አሳቡ ይህ ትምህርት አማኞቹ ጌታን ከማወቃቸው በፊት የነበረውን የቀድሞውን ትምህርት የሚያመላክት ነው። በቆላስይስ የነበረውም ትምህርት ጥሪ የሚያደርግላቸው በክርስቶስ እንዲጸኑ ሳይሆን ወደ ኋላ እንዲመለሱ የሚጋብዝ ነበር ማለት ነው። በስተ መጨረሻም እንደዚህ ያለው ትምህርት ከንቱና የሚያታልል ፍልስፍና ነው። **<u>የሚያታልል የሚለውን ቃል እዚ ጋ ልብ ማለት ይጠቅማል።</u>** የሚያታልል ነገር እውነት የሚያዋጣ የሚመስል፣ ነገር ግን እውነታው ሲታይ **ውሸት የሆነ ነገር ነው።**

እዚህም ጋ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለው ነገር በቆላስይስ ያንጃበበውና እንዲጠነቀቁ የተነገራቸው ይህ ትምህርት፣ የሚያዋጣ መስሎ የሚመጣ ግን ውሸት የሆነ ፍልስፍና ነው። <u>**ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ "ከንቱ"፣ይለዋል።**</u> ሲሰሙት ልብ ይማርካል ሲይዙት ግን ባዶ ነው። ለደህንነት አይሆንም፣ እግዚአብሔርን ለመመሰል አይረዳም። ስለዚህም በእንደዚህ ያለው ትምህርት እንዳይማረኩ ያሳስባል።

**ከቁ 9-10** ለምን በክርስቶስ ብቻ መተከል፣ ማደግና መጽናት እንዳለባቸው ነገር ግን የሃሰት የሆነውን ይሻላል ብለው ለምን መከተል እንደሌለባቸው ይናገራል። "**በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና። ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ ሆናችሁ ተሞልታችኋል**" (ቆላ 2: 9-10) ። በመጀመሪያ ክርስቶስ በራሱ እግዚአብሔር ነው። ሙሉ መለኮት በሰው ሰውነት ውስጥ ተገልጦ የሚኖርበት እግዚአብሔርም ሰውም ነው። በሁለተኛ ደረጃ በቆላስይስ የነበረው የስህተት ትምህርት መላዕክትን ወይንም መንፈሳዊ አካላትን (አለቅነትንና ሥልጣናትን) እንዲያመልኩ የሚያበረታታ ነበር። ክርስቶስ ግን የሥልጣን ሁሉ ራስ ነው። በእርግጥም ከዚህ በፊት ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ የጻፈውን ካስታወስን ከክርስቶስ ኢየሱስ የሚበልጥ ነገር የለም።

**ከቁ 11-15** ባለው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች በክርስቶስ ሙሉ ሆነው ወደ እግዚአብሔር እንዴት እንደቀረቡ ያሳያል። በመጀመሪያ አማኞቹ "**በእጅ ባልተደረገ መገረዝ**" ተገርዘዋል። በቆላስይስ የነበረው አስተምህሮ፣ የተወሰነው የአይሁድ ቅይጥ ስለነበረ መገረዝን የሚያዝ እንደነበረ በመግቢያችን ላይ ተመልክተናል። ነገር ግን ይህ መገረዝ በእጅ የሚደረግና በሥጋ ሰውነት ላይ የሚፈጸም መገረዝ ነው። ከዚህ ውጪ የሚገረዘው ግለሰብ እግዚአብሔርን እንዲፈራ፣ እንዲከተል ወይንም በእርሱ ፈቃድ እንዲኖር አያደርገውም። በክርስቶስ የሚገኘው መገረዝ ግን እውነተኛ ነው። ግርዘቱም የሥጋ ሳይሆን የልብ መገረዝ ነው። <u>**እዚህ ጋር ሐዋርያው ጳውሎስ "የሥጋ ሰውነትን በመግፈፍ" ነው የሚለው። ሆኖም ግን የሥጋ ሰውነት ሲል የሥጋ ምኞትን፣ ወይንም የኃጢአት ተፈጥሮን ለማለት እንደሆነ ልናስተውል ይገባል።**</u> በአዲስ ኪዳን ሥጋ የሚለው ቃል አሮጌን ማንነት፣ የኃጢአትን ተፈጥሮ ሊያመለክት ይችላል። ስለዚህም ሰው

በክርስቶስ ሲሆን አንደኛው የሚያገኘው ነገር እውነተኛ ግርዘትን ማለትም ኃጥያት የማድረግ መሻት መቆረጥ ነው። በተጨማሪ **በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር በመሞትና በመነሳት ምሳሌ አዲስ ሕይወትን ተቀብለዋል። ይህም የኃጢአትን ይቅርታ በማግኘት የትንሳኤ ምሳሌ ሆኖ ያገለግላል (12-13)። ይህን ክፍል አንዳንዶች የውሃ ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ትምቀት ነው ብለው ቢተረጉሙም ብዙዎች አይቀበሏቸው።**

በመጨረሻ በቁ 14 እና 15 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በአማኞችና በእግዚአብሔር መካከል የሚቆሙትን ሁለት እንቅፋቶች እንዴት በክርስቶስ መስቀል እንዳስወገዳቸው ይነግረናል። **የመጀመሪያው "በትዕዛዝ የተጻፈው የዕዳ ጽህፈት"** ነው። በቁ 14 ላይ ይህንን የዕዳ ጽሕፈት እግዚአብሔር በክርስቶስ መስቀል "ደመሰሰው" ይለናል። **ሁለተኛው** "አለቅነትና ስልጣናት" ናቸው። ምናልባትም ይህ የክፉ መንፈሳዊ ስራዊትን ሳያመለክት አይቀርም። እነዚህን ደግሞ ትጥቃቸውን አስፈትቶ፣ በመስቀሉ ድል ነሳቸው ይለናል። አማኞችም የእግዚአብሔርን ሕግጋት በመጣሳቸው የሚከሰሱበት የዕዳ ጽህፈት ይኖራል (ይህ ሲባል የምር በእጅ የተጽፈ ክስ አለ ማለት አይደለም… ነገሩ ምሳሌ መሆኑን እናስተውል)። ይህንን ካለ በኋላ ሐዋርያው ጳውሎስ በሚያስገርም ሃረግ ክፍሉን ይጨርሳል "**ድል በመንሳት በእርሱ (በክርስቶስ ወይንም በመስቀሉ) እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።**" ይህ በድሮ ጊዜ አንድ ጀነራል የጠላት ወታደሮችን ማርኮ ወደ አገሩ ሲመለስ የአገሬው ሰው ወጥቶ ይቀበለዋል። ጀነራሉ የማረከውን ምርኮ ከኃላ አስከትሎና ለህዝቡ እያሳየ ያልፋል። እግዚአብሔርም በክርስቶስ መስቀል ድል ያደረጋቸውን አለቅነትንና ስልጣናት እንደዚህ ነው ያደረጋቸው ይለናል። በማይመስል ነገር በመስቀል ሞት እግዚአብሔር አለቅነትንና ስልጣናትን አሸነፈ። ግን እያዞረ በግልጥ አሳያቸው የሚለው ነገር ለማን እንዳሳያቸው ግልጽ አይደለም። **ቁም ነገሩ ግን አማኞች በክርስቶስ በሕይወቱ፣ በሞቱና በትንሳኤው እንዲያተርፉና ሙሉ እንዲሆኑ ሆነዋል። ስለዚህም በፍጹም በፍጹም በሌላ ትርጉም በማይሰጥ ቀፎ ትምህርት ሊታለሉና ሊማረኩ አይገባም።**

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቆላ.2፡6-7 በማንበብ አማኞች በክርስቶስ ማደግና መጠንከር እንዳለባቸው ለማሳየት ሐዋርያው የተጠቀመባቸው ቃላትና ምሳሌዎችኝ ምንድ ናቸው?
2. ቆላ 2፡7 እና 8 ላይ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ወይም ምክር ምንድ ናቸው? የሁለቱን ቁጥሮች ልዩነት ተወያዩ? ለቁጥር 8 ትኩረት ይሰጥ።
3. በቆላ.2:9-10 በማንበብ የተረዳችሁትን አካፍሉ። ቆላ.1:15 ይነበብ።
4. በቆላ 2፡11-15 ባለው ክፍል ክርስቶስ ብቃታቸው መሆኑን የተገለጸበትን መንገድ አስረዱ? ከቆላስይስ መልዕክት አጠቃላይ ዓላማ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
5. በቆላ 2:12 በጥምቀት ከጌታ ከኢየሱስ ከእርሱ ጋር መቀበርና መነሳት የተገለጸውም እውነት ተወያዩ (ሮሜ 6:2-5)።
6. ቆላ 2፡14 እና 15 ላይ ስለ ተከፈለልን ዋጋ እና ስለ ድነታችን የተገለጸው በምን መልኩ ነው? ይህስ ክርስቶስ ብቃታች ስለ መሆኑ ምን ያስተምረናል?
7. ከዛሬው ጥናት ምን እንደተረዳን አካፍሉ።
8. እስከሚቀጥለው የጥናት ክርስቶስ ብቃታችን መሆኑን ለአንድ አዲስ ሰው አካፍሉ፤ስንመጣ እንመስክር።

**መደምደሚያ፡-**

ለመዳን ከክርስቶስ ሌላ ተጨማሪ ነገር መኖሩን የእግዚአብሔር ቃል በፍጹም አያስተምርም። ክርስቶስ ብቻ!እርሱ ብቻ! በቂ ነው! ለመጨመር ለሚታገሉ ሰዎች እንንገራቸው።

# ጥናት ዘጠኝ

# የሰው ሥርዓተ-ትምህርትና ወግ/ልማድ አይጠቅምም

# የንባብ ክፍል ፡ ቆላ 2:16-23

**ዓላማ**

አማኞች የሰውን የፍልስፍና እና ሥርዓት ባለመከተል በክርስቶስ ብቻ ፍጹምና ሙሉ መሆናቸውን በማወቅ በእርሱ እንዲበረቱና እንዲያድጉ ማሳሰብ

**መግቢያ**

ባለፈው ጥናታችን እንደደመደምነው ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብና ድነትን ለማግኘት ከክርስቶስ ሌላ አያስፈልገውም። ክርስቶስ እንደኛው ሁሉ ሰው ሆኖ ሳለ ግን ደግሞ የመለኮት ሙላት ሁሉ የተገለጠበት አምላክም ነው (ቆላ 2:9,1:19-20፤1ዮሐ.5:20)። ስለዚህም ሰውንና እግዚአብሔር ማገናኘትም ማስታረቅም የሚችል ብቸኛ አምላክ ነው።

**ነገር ግን ከውጭ ሲታዩ መንፈሳዊ የሚመስሉ፣ ሥርዓታቸውና ወጋቸው የሚማርኩ ልምምዶችስ እንዴት ነው የሚፈረጁት የሚል ጥያቄ ይነሳ ይሆናል። ያ ሁሉ ሥርዓት፣ ያ ሁሉ ብሕትውና (ባህታውነት)፣ ያ ሁሉ መንፈሳዊ ልምምድ፣ ከንቱ ነው ማለት ነው? ለአማኝ ብቃቱ በክርስቶስ ከሆነ ሌሎችስ ልምምዶች?**

ሐዋርያው ጳውሎስ ባለፈው ካየነው አሳብ በመቀጠል፣ ከ ቆላ 2:16-23 ባለውም ክፍል ወደ እግዚአብሔር ለመድረስና ለመዳን ክርስቶስ ብቻ እንደሚበቃ ለማሳየት ሌሎች ሥርዓቶችና ልምምዶች ሁሉ ከንቱ መሆናቸውን ያሳያል። ሰው **ድነት የሚያገኝበት እየመሰለው፣ ሊጾም፣ ሊመጸውት፣ መልካም መስሎ የሚታየውን ሁሉ ሊያደርግ፣ አልፎም ራሱን ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ሥራ የለየ መስሎት ገዳምም ሊገባ ይችላል።** ሆኖም ግን በዕለቱ መጨረሻ እነዚህ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር አያቀርቡም ምክንያቱም ለሰው ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ ብቸኛ ብቃቱ ክርስቶስና ክርስቶስ ብቻ ነው።

ስለዚህ ሰው ራሱን መጀመሪያ መጠየቅ ያለበት ክርስቶስ አለኝ ወይ ብሎ ብቻ ነው! ላመነና ክርስቶስ ላለው ሰው ሌላ ምንም አያስፈልገውም። ማንም እንደማይድን አድርጎ እንዲፈርድበት ሊፈቅድ አይገባውም። ይልቁንም በጌታው ረክቶና ተደላድሎ እንዲኖር ይገባዋል (ቆላ.2:20-23)።

**ትንታኔ (ማብራሪያ)**

ከላይ በመግቢያው ላይ እንደጠቀስነው ባለፈው ጥናታችን (ማለትም በቆላ 2:6-15) ክርስቶስ ኢየሱስ ፍጹም ለድነታችን ብቁ መሆኑን አይተን ነበር። በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ መኖሩ ብቻ ሳይሆን፣ **<u>እኛም በእርሱ ሆነን ሙሉ ተደርገናል።</u>** በእርሱ የኃጢአትን ይቅርታ መቀበል ብቻ ሳይሆን፣ **<u>ከኃጢአት ባርነት ነጻ ወጥተናል።</u>** በእርሱ የሚከሰን ህግም ተደምስሷል። ከዚያም አልፎ ከክርስቶስ ጋር ሞተን በመነሳታችን፣ በአዲስ ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን መኖር እንድንችል ተደርገናል።

ሆኖም እስካሁን ባየነው ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይናፈሱ የነበሩትን የሀሰት ትምህርቶችን ጠቅሶ ጉድለታቸውን አላሳየም። በዛሬው የጥናት ክፍል ሐዋርያው ጳውሎስ የቆላስይስ ቤተ ክርስቲያንን ከእውነት ለማውጣት ያሰፈሰፉትን ሦስት አስተምህሮዎችን በትክክል እያነሳ በእነርሱ በእርግጥ ድነት እንደሌለ ያሳያል።**1ኛ/ ከ 16 -17 ባለው የአይሁድን ሥርዓት መጠበቅ እንዳለበት የሚያስተምሩትን ያነሳል። 2ኛ/ከቁ 18-19 የመላዕክት አምልኮ መደረግ እንዳለበት እና 3ኛ/ ምስጢራዊ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ አስፈላጊ መሆኑን የሚሰብኩትን ያነሳል። 4ኛ/ በስተመጨረሻም ከቁ 20-23 ብህትውና ወይም ባህታውነት ልክ አለመሆኑን በማስረዳት ይጨርሳል።**

በቁ. 16 ላይ የአይሁድ ሥርዓትን መጠበቅ አለበት የሚሉ አስተማሪዎች መኖራቸውን የሚጠቁም ነገር ያሳየናል። ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ስርአቶች ካልጠበቃችሁ ብሎ "**ማንም አይፍረድባችሁ**" ሲል በእርግጥ ይህ መደረግ አለበት ብለው የሚሞግቱ እንዳሉ ያመለክታል። መጠበቅ አለባቸው የተባሉት ሥርዓቶች መብልንና ቀናትን የተመለከቱ ናቸው። በብሉይ ኪዳን

እንደምናውቀው ሕዝበ እስራኤል ለመብልና ለመጠጥ የተፈቀዱላቸውና ያልተፈቀዱላቸው ነገሮች ነበሩ።

ከዚህም ባሻገር በዓመት አንዴ የሚያደርጉት በዓል (ለምሳሌ የዳስ በዓል)፣ በወር አንዴ የሚደረገ (ለምሳሌ መባቻ) እንዲሁም በሳምንት አንዴ የሚከበር ቀን (ለምሳሌ ሰንበት) ነበራቸው። እንግዲህ እነዚህን ሥርአቶች ካልጠበቃችሁ የሚሉ ወግና ልማድ አጥባቂዎች አማኞችን ሳያደናግሩ አልቀሩም። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን "**እንግዲህ** (ማለትም ብቃታችሁ ክርስቶስ ከሆነ) **በመብል ወይንም በመጠጥ፣ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይንም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ**" ይላል።

በቁ 17 ላይ በእነዚህ የአይሁድ ሥርዓቶች አማኝ ራሱን ለምን ማስገዛት እንደሌለበት ወይንም ሌላ ሰው ብቁ እንዳልሆነ አድርጎ እንዲፈርድበት መፍቀድ እንደሌለበት ይገልጻል።"**እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፣ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።**" <u>በሌላ አባባል እነዚህ የአይሁድ ሥርዓቶች ቀድሞውንም ቢሆን ዋና ነገር አልነበሩም ነገር ግን ወደፊት ሊመጣ ላለው ነገር የሚያዘጋጁ ጥላ ብቻ ነበሩ ማለት ነው</u>። ዋናው ነገር ግን አሁን ክርስቶስ ሲመጣ ተገልጧል። ይህ የአይሁድን ሥርዓት መጠበቅ የማያስፈልግ መሆኑን ብቻ ሳይሆን እውነተኛው ነገር በክርስቶስ በመገኘቱ ክርስቶስ ብቃታችን እንደሆነ ያመለክታል። ይህ ትምህርት በገላቲያ የነበሩትን አማኞች ያባብል የነበረ ሀሰተኛ ትምህርት ነው።

በቁ 18 እና 19 ላይ በቤተ ክርስቲያኑ ሌላው የሚናፈሰውን አስተምህሮ ያነሳል። "**ትሕትናና የመላዕክትን አምልኮ እየወደደ ባላየውም ያለፈቃድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ**" ይላል። እዚህ ቁጥር ውስጥ ለመረዳት የሚያስቸግሩ ብዙ ነገሮች አሉ ሆኖም ግን አሳቡ ግልጽ ነው። የመላዕክትን አምልኮ የሚያስተምሩና ምስጢራዊ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ (mysticism) እያደረጉ ራሳቸውን መንፈሳዊ እንደሆኑ ቆጥረው የሚታበዩ እንዲሁም ሌላውን ብቁ እንዳልሆነ የሚቆጥሩ ነበሩ። ምናልባት እዚህ ጋ የክፍሉን

አሳብ በሚገባ ለመረዳት አዲሱ መደበኛ ትርጉምን መመልከት አስፈላጊ ይሆናል። በድሮው ትርጉም "ባለየውም ያለፈቃድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ" የሚለው ሀረግ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም "እንደዚህ ያለው ሰው ስላየው ከመጠን በላይ ራሱን እየካበ በሥጋዊ አእምሮው ከንቱ አሳብ ተሞልቶ ይታበያል" በሚል ተተርጉሟል። ይህንን ትምህርት የሚያናፍሱት ሰዎች ምናልባትም ባለን መንፈሳዊ ልምምድ ራዕይ እናያለን እያሉ ሳይታበዩ አልቀሩም። <u>**እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔር ፍጹም ቅዱስ በመሆኑ እና እርሱ ጋር ርኩስ የሆነ ሥጋን የለበሰው ሰው መድረስ ስለማይችል ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኙ ተዋረድ ያላቸው መላዕክቶች አሉ የሚያስተምሩ ኖስቲሳዊያን (Gnostics) ናቸው።**</u> ስለዚህም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያገናኙት እነዚህን መላዕክት ማምለክና የእነርሱን እርዳታ መሻት አለበት። ይህ ከውጭ ለሚያየው በእርግጥ ትህትና ይመስላል - ትልቁን እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚቻለው በትህትናና በመላዕክት አማላጅነት መቅረብ ነው ይላሉ። አዲሱ መደበኛ ትርጉም ይህንን "ዐጉል ትሕትና" ይለዋል። ይህንን በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች የሚሰጠው ማሳሰቢያ እንዲህ ያሉ ሰዎች አይፍረዱባችሁ ወይንም "**እንዳያደናቅፋችሁ ተጠንቀቁ**" ነው። በሌላ አባባል የጌታን መንገድ እየተከተሉ ሳሉ ይህንን ዓይነት ምስጢራዊ ልምምድ አለን የሚሉ አሳቾች ከመንገድ የወጡ ወይንም የሳቱ እንደሆኑ እንዲነግሯቸው አያስፈልግም።

እንዲህ ያለ አጉል ትምህርት የሚያስተምር ሰው ለምን መስማት እንደሌለባቸው **በቁ 19** ላይ በግልጽ ያሰፍራል። "እንዲህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም"። እዚህ ጋር ራስ የሚለው ክርስቶስን እንደሆነ ግልጽ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ክርስቶስ ራስ እንደሆነ ወደ ሁለት ጊዜ መጥቀሱን እናስታውሳለን። ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው **(ቆላ 1:18)** እንዲሁም ለአለቅነትና ለስልጣናት ሁሉ ራስ ነው **(ቆላ 2:10)።** እንዲህ ያለውን ትምህርት የሚያስተምር ሰው ትልቁ ችግሩ ከዚህ ሁሉ የመላዕክት አምልኮና ምስጢራዊ ልምምድ ሁሉ በኋላ ወደ ክርስቶስ አለመድረሱ ነው። ለፍቶ ደክሞ ያለምንም

ዋጋ ይቀራል ማለቱ ነው! ክርስቶስ ራስ የሆነለት አካል (ቤተ ክርስቲያን)፣ "**እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል**" ምክንያቱም ይህ ክርስቶስ ራስ የሆነለት አካል በጅማትና በማሰሪያ ተያይዞ እንደ ጤነኛ አካል ምግብን እየተቀበለ እግዚአብሔር ደግሞ እድገትን እየሰጠው ራስ ወደ ሆነው ክርስቶስ ያድጋል። እንግዲህ የአይሁድ ሥርዓት ዋና ለሆነው ለክርስቶስ እውነት ጥላ ስለነበር ከክርስቶስ በኃላ ትርጉም የለውም፣ የመላዕክትም አምልኮና ምስጢራዊ ልምምድም ወደ ክርስቶስ ስለማያደርስ ጥቅመ ቢስ ነው።

ቀጥሎ **ባለው ከቁ 20 -23** ሌላኛውንና የመጨረሻውን አስተምህሮ ያነሳል። ይህ አስተምህሮ ብሕትውናን ወይም ባህታዊነት (Monasticism) የሚያስተምር ነው። ይህ "**አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካ**" የሚሉ ትዕዛዛትን የሚደነግግ ነው። በቁ 16 ከተገለጸው የአይሁድ ሥርዓት ይለያል ምክንያቱም የአይሁድ ሥርዓት ምንም አሁን ትርጉም ባይኖረውም በጊዘው በእግዚአብሔር የተደነገገ ሥርዓት ነበር፤ ይሄኛው ግን "**እንደ ሰው ሥርዓት እና ትምህርት**" የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። እዚህ ክፍል <u>**ላይ አትያዝ አንትቅመስና አትንካ**</u> የሚሉት ምንን እንደሆነ በግልጽ አልተዘረዘረም ሆኖም ግን ሰውነትን መጨቆን ተገቢ እንደሆነ በማመን የሚደረጉ ነገሮች ናቸው። ይህ በኖስቲሳዊያን (Gnostics) አመለካከት የሰው ሰውነት እርኩስ ሰው ከሚለው አመለካከት የመነጨ ነው። <u>**አንዳንድ ኖስቲሳዊያን ሰው ሰውነቱ እርኩስ በመሆኑ ይህ እርኩስ ሥጋ ምንም ቢሰራ ችግር የለውም ዋናው መንፈስ ነው እንጂ ሲሉ ሌሎች ደግሞ የለም የሰው ሰውነት እርኩስ በመሆኑ ሥጋ ያለ ልክ እንዳያስቸግር መጨቆን አለበት ብለው ያምኑ ነበር።**</u> ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንን ሁለተኛውን አመለካከት በመቃወም የሚጽፍ ይመስላል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህ አስተምህሮና ሥርዓት ፈጽሞ ተገቢ እንዳይደለ በሦስት ነጥቦች ያስረዳል። **አንደኛ** ክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር ሞቷል። አማኝ ጌታን ሲቀበል አንደኛው በሕይወቱ የሚከናወነው ነገር **ለአለም፣ ለሥጋ፣ ለሰይጣን መሞትና በአዲስ ሕይወት መነሳት ነው**። አማኝ ከክርስቶስ ጋር የሚሞተው፣ ለሕግና ለሰው ሰራሽ ሥርዓት ሁሉ ነው። ከክርስቶስ በኋላ ሰው የሚኖረው ለክርስቶስ ብቻ ነው። **ሁለተኛ፣** እነዚህ አትንካ አትቅመስና አትያዝ የመሳሰሉትን

የሚሉት ነገሮች "**በመደረግ ሊጠፉ**" የተወሰኑ ናቸው። በሌላ አባባል በሰው ሕይወት ውስጥ ዘላቂ የሆነ መንፈሳዊ ለውጥ የሚያመጡ ነገሮች አይደሉም። **ለምሳሌ "ውሻ አትንካ!" የሚል ትዕዛዝ ቢኖር ሰውየው ውሻ ካልነካ ትዕዛዙ ፍጻሜ ያገኛል። ሌላ ቀጣይ መንፈሳዊ ተጽዕኖ አያመጣም። "ቅጠል ብቻ ብላ!" የሚል ትዕዛዝ ቅጠል በመብላት ይፈጸማል ... አለቀ ማለት ነው።** ሌላ ቀጣይ ነገር የለውም። **በሦስተኛ** ደረጃ እንዲህ ያለው ሥርዓት "**እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፣ ነገር ግን ሥጋን ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም።**" የዚህ አይነቱ ሥርዓት ሌላኛውና አደገኛው ነገር ይህ ነው። በዚህ ዓይነት ለሚመላለሰው ሰው የአምልኮ ስሜትንና እውነተኛ ያልሆነ ትህትናን ይፈጥራል (አዲሱ መደበኛ ትርጉም ያነጻጽሩ)። **ከውጪ ለሚያየውም ሰው ይህ አይነቱ ብሕትውና ወይም ገዳም መሰል ሕይወት ጥበብ ያለበት ይመስላል። በእርግጥም ብዙ ሰዎች እንደዚህ በሚመስል ኑሮ ተማርከው ገዳም ይገባሉ። ነገር ግን እንዲህ ያለው አኗኗርና ልምምድ የሥጋን ልቅነት ለመግዛትና ሥጋን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለማስገዛት "ምንም" አይጠቅምም።** ይህ ሁሉ ከንቱ ድካም ነው። ሰው ሥጋውን መጨቆንና መግዛት የሚችለው አካላዊ ሰውነቱን ስላጎሳቆለ ሳይሆን በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ አሮጌውን ማንነት በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ሲገድል ነው። ያ አዳማዊ ባህሪይ ገዳም በመግባት፣ በብሕትውና፣ በመራብና በመጎሳቆል አይሞትም።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በቆላ 2:16 የሚናገረው ስለምንድ ነው? እንዲህስ ዓይነት ችግር በአሁን ዘመን በምን መልኩ ነው የሚንጸባረቀው?
2. በቆላ 2፡17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የተቃወመው የሀሰት ትምህርት ምንድ ነው? ለዚህስ የሰጠው ምላሽ ምንድን ነው?
3. ቆላ.2:16-18 በቆላስይስ ቤተክርስቲያን የነበሩትን ሦስት ዋና ዋና የሰው ሥርዓትና ወግ ነክ ትምህርቶች አብራሩ
4. በቆላ 2፡በቁ.19 መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን ሥርዓትና ወጎች ለመጠበቅ የሚታገል ሰው ችግሩ ምንድን ነው? ማስተዋል ያለበትስ ነገር ምንድ ነው?

5. በቆላ.1:22 መሠረት የአይሁድ ሥርዓት ምንድ ነው? ከክርስቶስ መምጣት በኋላስ ትርጉም የላቸውም የምንለው ለምንድን ነው?
6. ከላይ በማብራሪያው መሠረት ኖስትሳዊያን ስለ ሥጋና መንፈስ ምን አስተምህሮ እንዳላቸው አብራሩ? የዚህ ትምህርት ችግሩ ምንድ ነው? ማብራሪያውን ማንበብ ያስፈልጋል።
7. ቆላ 2:20-23 በማንበብ ተወያዩ። በአሁን ዘመን ካሉት ሀሰተኛ አስተምህሮ ጋር ምን ግንኙነት አለው?
8. በእንደነዚህ ዓይነት ትምህርቶች እና ልምምዶች ውስጥ ያሉትን ሰዎች በእውነተኛ ወንጌል እንዴት ልንደርስ እንደምንችል ተወያዩ። በበዓላት እና በልዩ ልዩ ማህበራዊ ኑሮ ህብረት ላይ ምን ማድረግ እንዳለብን ልምድ እንከፋፈል።

***መደምደሚያ***

በአጭሩ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ክፍል የሚለን ነገር ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ካመነ እግዚአብሔር ጋ ለመድረስ ወይም ህብረት ለማድረግ በክርስቶስ ምክንያት ብቁ ነው ። የአይሁድን ሥርዓት በመጠበቅ ሰው ወደ እግዚአብሔር አይደርስም ምክንያቱም እነዚያ ሥርዓቶች በክርስቶስ ለሚገኘው እውነት ጥላ ብቻ ስለነበሩ። መላዕክትን ማምለክና ምስጢራዊ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ማድረግ አይጠቅምም።ምክንያቱም ራስ ወደሚሆነው ወደ ክርስቶስ አያደርስምና። ብህትውናም ወደ እግዚአብሔር አያቀርብም። ምክንያቱም ሰውነትን በመጨቆን ሰው ውደ እግዚአብሔር አይደርስም። ደግሞም አማኝ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሥርዓት ሞቷል ... ዳግም እንዲህ ዓይነት ኑሮ ሊኖር አይገባም። ሰው በክርስቶስ ካለ በአይሁድ ሥርዓት ሳይታሰር፣ በመላዕክት አምልኮ ሳይሳተፍ፣ ራሱንም ሳያጎሳቁል በክርስቶስና በእርሱ ብቻ ወደ እግዚአብሔር መድረስ ይችላል። እርሱ ብቃታችን ነውና!

# ጥናት አሥር
# የክርስቶስን የበላይነት የሚያሳይ ህይወት መኖር (መሻትና ማስወገድ)
## የንባብ ክፍል ፡- ቆላ 3:1-9

**ዓላማ**

የክርስቶስን የበላይነት በህይወታችን እንድናሳይ ማሳሰብ።

**መግቢያ**

የክርስትና አስተምህሮ የአዕምሮ እውቀትን ብቻ የሚያዳብር ትምህርት እና ፍልስፍና የሚሰጥ ሳይሆን በእውነተኛ የሕይወት ጉዞ ውስጥ በተግባር ሊተረጎም የሚገባው እውነትን የሚያስተምር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በብዛት የመልዕክቶቹ የመጀመሪዎቹ ክፍል አስተምህሮ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ያስተማረውን መተግበር ነው።

በባለፉት ጥናቶቻችን እንዳየነው ክርስትና ክርስቶስ ብቃታችን እንደሆነ፣ ለድነትም ሌላ የሚያስፈልገን ነገር እንደሌለ አይተናል **(ቆላ 1:15,2:15-23)**። ስለዚህም ለድነት ሰው ቅጠል መበጠስ ወይም ጥምጣም መጠምጠም አያስፈልገውም። እንዲያውም ሰው ጌታን ካገኘ፣ ሌላው በሃይማኖት ስም ቀን መቁጠር፣ጥምጣም ጠምጥሞ፣ በብህትውና ስም ቅጠል በጥሶ፣ የሃይማኖትን ሥርዓትና ደንብ ጠብቆ የማያገኘውን አዲስ ሕይወት ያገኛል።

ሰው በክርስቶስ ሲሆን ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናል። ክርስቶስ እንደሞተ እሱም ከጌታው ጋር አብሮ ሞቷል፣ ክርስቶስ እንደተነሳ እሱም ለአዲስ ሕይወት ተነስቷል። ግን ጥያቄው ይህ እውነት እንዴት ነው በሕይወታችን የሚተረጎመው? ክርስቶስ ብቃታችን ነው ካልን እንዴት ነው በተግባር የሚታየው? ከሌላውስ ኃይማኖት እና ፍልስፍና በምንድን ነው የምንለየው? ይህንን የመሰለውን ጥያቄ ሐዋርያው ጳውሎስ (**በቆላ.3:1-4:6**) ባለው ክፍል መልስ ይሰጣል። በዛሬው ጥናታችን (**ቆላ.3፡1-9**) ያለውን ክፍል እናያለን።

**ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የክፍሉን ትንታኔውን(<u>ማብራሪያውን) በግላችን አንብበን ከሆነ ወደ መወያያ ጥያቄዎች መሄድ እንችላለን</u>**

**ትንታኔ (ማብራሪያ)**

የመጀመሪያውን ክፍል ማለትም **ቆላ.3፡1-9** ያለውን ክፍል ስናይ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚያሳስበን ጌታን ካገኘን ወዲህ ሕይወታችን ከድሮው አልባሌ ሕይወት ፈጽሞ ሊለይና እግዚአብሔርን የሚያሳይ ሕይወት ሊኖረን እንደሚገባ ነው። ቆላ.3፡1-4 ባለው ክፍል ለአዲሱ ሕይወት መሆን የሚገባውን መሰረታዊ መመሪያ ያሳስባል። <u>**ያም ጌታን ካገኘን በኋላ መሻታችንና አሳባችን ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ሊሆን እንደሚገባ ያስተምራል።**</u>

ክፍሉን ሲጀምር “ **እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ…”** በማለት ነው። ከዚህ ከፍ ብሎ ቆላ 2:20 ላይ **“ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ፣ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ** …” በማለት አማኞች ከክርስቶስ ጋር መሞታቸውን አሳስቦ ነበር፣ አሁን ደግሞ መሞት ብቻ ሳይሆን ከክርስቶስ ጋር መነሳታቸውን ያሳየናል። <u>**መሞታቸው ከአለማዊ ትምህርትና ስርአቱ ለመለየት ነው (2:20-22)**</u>። አሁን ግን መነሳታቸው ለአዲስ ሕይወት ነው። በዚህም አዲስ ሕይወት መሻታቸውና አስተሳሰባቸው ከድሮው የተለየ ነው። “**በላይ ያለውን እሹ፤ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።**” እዚህ ጋ መሻትና ማሰብ በሚሉት ቃላቶች መካከል ያለውን ልዩነት ልብ ማለት ይገባል። “መሻት” ጥማትን፣ ፍላጎትን የሚያሳይ ነገር ነው። <u>**ማሰብ ግ**</u>ን ነገርን ማብሰልሰል፣ ለነገሮች መፍትሄ በአዕምሮ ማውጣትና ማውረድን ያመለክታል። አማኝ የተጠራው ጥማቱ መንፈሳዊ እንዲሆን ብቻ ሳይሆን ነገሮችን የሚያስብበትና የሚያመዛዝነው ሰማያዊ ወይንም መንፈሳዊ በሆነ መንገድ እንደሆነ ያሳየናል። ሰማያዊ ነገርን <u>**መሻትና ማሰብ**</u> ነው የሚገባን ሲል ግን ለነገሩ አጽንኦት ለመስጠት **“በምድር ያለውን አይደለም”** ይላል። ይህ አባባል ትንሽ ግር ሊያሰኝ ይችላል። ለምሳሌ በምድር ላይ የምንሰራው ቤት ምድራዊ እንዲሁም እዚሁ ቀሪ ነው። ግን

ሐዋርያው ጳውሎስ ምድራዊ ስለሆነ ቤት አትስሩ የሚል መልዕክት እያስተላለፈ አይደለም። ማለት የፈለገው ምድራዊ (ዓለማዊ) መሻትን ነው። ይህ መሻት ከታች ወረድ ብሎ ከቁ 5 ጀምሮ ተዘርዝሯል። ስለዚህ እንደ ሰው ሁሉ ቤት ሰርተን ብንኖርም፣ መሻታችን ግን ምድራዊና እዚሁ ቀሪ ብቻ አይደለም የአማኝ ጥማቱ መንፈሳዊና ሰማያዊ ሊሆን ነው የሚገባው። በምድር የሚኖረው ምድራዊውን ሃብት፣ እውቀትና ችሎታ ሁሉ ለሰማያዊው ነገር ማዋል ይችላል። ለዚህም ምክንያት አለው። ሐዋርያው ጳውሎስ **"ሞታችኋልና ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሯልና"** ይላል። ድሮ ድሮ ከጌታ በፊት የአማኝ መሻት ምድራዊ ስኬትና አለማዊ ሕይወት ብቻ ነበር። አሁን ግን አማኝ ለዚያ ሲሞትና ጌታን ተቀብሎ የማትታየዋ ቤተክርስቲያን አካል ሲሆን፣ አሁን በዓይን አይታይም እንጂ በክርስቶስ አካል ውስጥ ተሰውሯል።

አማኝ ዛሬ ሰው ሁሉ ጋር ሲኖር እውነተኛ ማንነቱ እንዲሁም በክርስቶስ አካል ውስጥ ተሰውሮ መኖሩ አይታይም። ግን ጌታ በሚገለጥበት ጊዜ "የዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ" ይላል።

ከቁ 5-9 ባለው ምድራዊ የተባለውን ነገር እንዴት ማስወገድ እንዳለባቸው በሁለት ማሳሰቢያዎች ያስተምራል። **አንደኛ ብልቶቻችሁን ግደሉ** (ቁ. 5)፣ **ሁለተኛ የሚያሳፍር ንግግር** … እነዚህን ሁሉ አስወግዱ(ቁ. 8) ይላል። እነዚህ ሁለት ትእዛዛቶች ክርስቲያን ሊኖረው የሚገባውን ሥር ነቀል ለውጥ የሚያሳስቡ ናቸው። ግደሉ የሚለው "**በምድር ያሉ ብልቶቻችሁን"** ነው። በእርግጥ የሰውነት አካላቶቻችንን እንድንቆርጥ፣ እንድናጎሳቁል የሚመክር አይደለም። ነገር ግን በሰውነት አካላቶቻችን የሚሰራውን ክፉ መሻት እንድንቆርጥ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም በምድር ያሉትን ብልቶቻችሁን ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ሲያብራራ **"እነዚህም ዝሙት እና እርኩሰት፣ፍትወትም፣ ክፉ ምኞትም፣ ጣዖትን ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው"** ይላል።

ይህ ክፉ መሻት ተገቢ እንዳልሆነና ክርስቲያን ከሕይወቱ ሊነቅለው የሚገባ መሆኑን በሁለት መንገድ ሐዋርያው ጳውሎስ አሳስቧል። **አንደኛ ይህ አይነቱ ሕይወት፣ ትክክል ስላይደለ የእግዚአብሔርን ቁጣ ያመጣል (ቁ. 6)።** ይህንን ዓይነት ሕይወት የሚለማመድ አማኝም ሆነ የማያምን፣ በዚህ ዘመንም ይሁን በዘመን መጨረሻ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣበታል።[12] **ሁለተኛ ሰው ጌታ ከማግኘቱ በፊት ይመላለስበት የነበረ ሕይወት እንጂ ዛሬ ሊገዛለት የሚገባው ሕይወት አይደለም** (ቁ.7)።

ከመግደል ጋር በተያያዘ አስወግዱ የሚለው የማይገባን ንግግር ነው (ቁ.8)። ይህንንም የማይገባ ንግግር ሐዋርያው ጳውሎስ ዘርዝሮታል … **"ቁጣንና ንዴትን፣ ክፋትንም፣ ከአፋችሁም ስድብን፣ የሚያሳፍንም ንግግር"** ሲል። በቆላ.3፥8 ላይ ያልተዘረዘረ ግን አማኝ ሊያስወግደው የሚገባውን የአንደበት ጉዳይ ቁ 9 ላይ ይገልጻል። **"እርስ በእርሳችሁ" ውሸት አትነጋገሩ" ይላል።** እዚህ ጋር ሐዋርያው ጳውሎስ አማኞች መሻትን ብቻ ሳይሆን ከመሻትም አልፎ ከአንደበት የሚወጣውን ንግግር አማኝ ሊቆጣጠር እንደሚገባ ያመለክታል።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ቆላ 3፥1 ላይ "...ከክርስቶስ ጋር ከተነሳችሁ ..." ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ቆላ 3፥1-2 "በላይ ያለውን **እሹ"** እና "በላይ ያለውን **አስቡ"** በእነዚህ በሁለቱ ነገሮች መካከል እንድነት እና ልዩነት አለ? ተነጋገሩ
3. ቆላ 3:5 ላይ "ስለዚህ ምድራዊ ምኞቶቻችሁን ግደሉ…" ይህ ማለት ምን ማለት ነው? በዚህ ክፍል **"ስለዚህ…"** የሚለው አገናኝ ቃል ምን ጥቅም አለው?
4. ከላይ በተነጋገርነው ሀሳብ መሠረት ሥጋችንን መጨቆን እና ማጎሳቆል በመንፈሳዊ ህይወታችን የሚጨምረው ፋይዳ ይኖራል ትላላችሁ? ለምን?

---

[12] በድሮው ትርጉም "በማይታዘዙ ልጆች ላይ" ተብሎ በቁ 6 ላይ የተተረጎመው በማይታዘዙት ላይ ብቻ ተብሎ ሊተረጎም ይገባል። በትክክለኛው ቅጂ ላይ "ልጆች"፡የሚል ቃል የለም። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚገለጠው በማይታዘዙ ልጆች ላይ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በማይገዙ ሁሉ ላይ ነው።

5. ቆላ 3:6-7 **“በእነዚህም ምክንያት (ቁ.6) …** እነዚህ (ቁ.7)…” የተባሉት ነገሮች ምንድ ናቸው? በዚህ ክፍል እንደ ውጤት የተነገረው ምንድ ነው?
6. ቆላ 3፡8 ላይ አስወግዱ የተባለው ምንድን ነው ? በቁ 5 ላይ ግደሉ ከሚለው ጋር በምን ይገናኛል?
7. ከዛሬው ጥናታችን ብቃታችን የሆነውን ክርስቶስን ለመግለጽ ምን ተማርን?
8. በእነዚህ ነገሮች (ቁ.5 እና ቁ.8) የምንፈተን ብንኖር ጌታ ልረዳን ስለፈለገ ዛሬ ራሳችንን እያየን እንጸልያለን?

***መደምደሚያ***

ከክርስቶስ ጋር ሞተን ከእርሱ ጋር ከተነሳንና አዲስ ፍጥረት ከሆንን ከርስቶስ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን ማሰብና ማሰላሰል የሚጠበቅብን ሲሆን በአንጻሩም በምድር ያሉትን ብልቶቻችንን በየዕለቱ መግደል ይጠበቅብናል።

# ጥናት አስራ አንድ

# “የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል ... አዲሱን ሰው መልበስ”

# የንባብ ክፍል፡- ቆላ 3:10-17

**ዓላማ**

<u>አማኙ የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል አዲሱን ሰው ማለትም ክርስቶስን እየለበሰ በየዕለቱ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል በአዕምሮው ሲታደስ በአንጻሩ የድሮ ማንነቱ እየጠፋ እንደሚሄድ ለማሳየት።</u>

**መግቢያ**

በመጀመሪያ የሰው ልጅ ሲፈጠር በእግዚአብሔር **መልክ እና ምሳሌ** እንደሆነ ቃሉ ይነግረናል (ዘፍ 1:26-27)። ይህ መልክ እና ምሳሌ በኃጢአት ምክንያት ተበላሽቷል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ሀሳብ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ያንጸባርቃል ማለትም እንዲህ በማለት “የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል በዕውቀት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችኋል” (ቆላ 3:10)፣ይህ የእግዚአብሔር እቅድ ነው። <u>የዚህ መልክ እና ምሳሌ ትርጉሙ የእግዚአብሔርን የሥነ ምግባር (morality) ባህሪይውን እና ምክንያታዊነትን (rationality or logic) የሚያሳይ ነው፤ “ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ” (ኤፌ 4:24)።</u> የሰው ልጅ በነፍሱ ስሜት፣እውቀት እና ፈቃድ አለው። ስለዚህ አዲሱ ሰው በምግባረ-ባህሪይና በምክንያታዊነት ዕውቀቱ እግዚአብሔርን እንዲመስል ያስፈልጋል። ይህ ማለት ደግሞ ሰው አምላክ ነው ማለት አይደለም (ዮሐ 4:24)። በሁሉን ቻይነቱ፣ በሁሉን አዋቂነቱ፣ በሁሉ ቦታ መገኘቱ እና በሉዓላዊነቱ ጌታን አይመስልም። **ቆላ.3፡15-17** ደግሞ የአዲሱን ሰው ባህሪይ ወደ ጎን እና ወደ ላይ ያለውን ግንኙነት ያስረዳል። ይህ ሁሉ ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ይሁን በማለት አሁንም ክርስቶስን ያመጣል።

***ትንታኔ/ማብራሪያ***

ለምንድን ነው ሰው <u>**ምድራዊ (አለማዊ) መሻቱን**</u> መግደልና ማስወገድ የሚያስፈልገው የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ሐዋርያው ጳውሎስ **ከቁ 10-11** ባለው አጭር መልስ ይሰጣል። **አንደኛ "አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና"፣ ሁለተኛ "የፈጠረውን ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል"** ይላል። አሮጌው ሰው የሚለው ከጌታ በፊት የነበረውን በምድራዊ መሻት የተሞላውን የድሮውን ማንነት ነው። ሆኖም ከላይ እንዳየነው ያ ማንነት ከክርስቶስ ጋር ሞቷል። ያንን ማንነት ክርስቶስን በመቀበል ገድለነዋል። ግን ክርስትና የሞት ብቻ ሕይወት ሳይሆን የትንሳኤም ሕይወት ነው። ስለዚም አማኝ ከጌታ ጋር ለአዲስ ሕይወት ተነስቷል። ያ አዲስ ሕይወት አዲሱ ሰው ይባላል። አማኝ በአዲስ ሕይወት ሲኖር በእርግጥ አሮጌውን ማንነት ሊገድል፣ ሊያስወግድ ይገባል። እንደገናም አዲስ ልብስ እንደ ለበሰ ሰው ሊመላለስ ይገባል (ቁ.10)።

ይህ አዲስ ሰው፣ ያለ ዘር ያለ ነገድ፣ ያለ ጾታ፣ ያለ ኑሮ ደረጃ ልዩነት የለበሰው ሁሉ ሊኖርበት የሚገባ ሕይወት ነው። ይህ አይነቱ ልዩነት ያለው በማያምን ዘንድ ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ግን አዲስ ሰው አዲስ ነው ያለ ልዩነት።

እንግዲህ የመጀመሪያው ክፍል ከቁ 1-9 ያለው ክፍል አዲስ ማንነት በማግኘታችን መሻታችን ምድራዊ (አለማዊ) ሳይሆን ሰማያዊ መሆን እንዳለበት ያስገነዝበናል። **ሁለተኛው** ክፍል ከቁ 10-17 ያለው አዲሱ ሰው እንዴት ነው የሚመላለሰው የሚለውን ያስገነዝበናል (አስወግዱ እና ልበሱ)። ባለፈው ያው አሮጌው ሰው ምን ዓይነት ሕይወት እንደሆነ ገልጿል። አሁን ግን አዲሱ ሰው ወይንም በዚህ ክፍል **"የእግዚአብሔር ምርጦች"** ተብለው የሚጠሩት እንዴት እንዲመላለሱ እንዲገባ ያሳስባል።

አሮጌውን ሰው በተመለከተ በቁ 5፣ 8 እንዲሁም 9 ላይ "ግደሉ"፣ "አስወግዱ" ወይንም "ገፋችሁታል" የሚሉ ቃላቶች ናቸው። ሐዋርያው ጳውሎስ የሚጠቀመው። አዲሱ ሕይወት ግን የማስወገድ፣ የመግፈፍና የመግደል

ብቻ ሳይሆን፣ የመልበስና መልካም የማድረግም ነው። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ በቁ 12 ላይ የመጀመሪያው ትዕዛዙ "**ልበሱ!**" የሚል ነው። ሰው የቆሸሸውን፣ ያረጀውንና የማይጠቅመውን ልብሱን አውልቆ ሲጥል፣ አዲስ ልብስ እንደሚለብስ ክርስትናም እንደዚሁ ነው። አሮጌውን ሰው ማውለቅ ብቻ ሳይሆን አዲሱን ሰው እንድንለብስ ነው የተጠራነው። የአሮጌው ሰው ስራ ባለፈው ከፍ ባለው ክፍል ላይ ተጠቅሷል አሁን ግን እንደ እግዚአብሔር ምርጦች አማኞች እንዲለብሱት የተጠሩት ምን እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ ይገልጻል፡- እነዚህም "**ምህረትን፣ ርኅራኄን፣ ቸርነትን፣ ትህትናን፣ የዋህነትን፣ትዕግስትን ልበሱ**"(ቁ.12)። ባጭሩ ለሌሎች መልካም ማድረግን ያሳስባል ወይም ግንኙነትን ያመለክታል። በመቀጠል ይቅርታንና ፍቅርን እንዲለማመዱ ያዛል። ስለ ይቅርታ ግን ሲናገር "**ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ**" ይላል። ይህ ማለት ይቅር ልንለው የማንችለው ዓይነት በደል ሊኖር አይገባም ማለት ነው።

ባጭሩ ከቁ 15 እስከ 17 ባለው ብቻ ከፍ ብሎ ከዘረዘርናቸው ውጪ ወደ 6 የሚጠጉ አዲሱን ሰው የለበሱ አማኞች ሊለማመዷቸው የሚገባ አካሄዶችን ይዘረዝራል።

1. የእግዚአብሔር ሰላም በልባችሁ ይግዛ
2. የምታመሰግኑ ሁኑ
3. የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ
4. እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገስጹ
5. ለእግዚአብሔር ዘምሩ
6. **የምታደርጉትን ሁሉ በኢየሱስ ስም አድርጉት።**

እነዚህ ሁሉ አማኞች የእግዚአብሔር ምርጦች እንደመሆናቸው ሊኖሩባቸው የተጠሩበት ሕይወት ነው። አሮጌው ሰው ሲገፈፍ፣ አማኝ ሊለብሰው የሚገባው ልብሶች ናቸው።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ቆላ.3፡10 ስናነብ "**... አዲሱን ሰው...**" የሚለውን የሚለውን ሀሳብ አብራሩ። አሮጌውስ ምንድ ነው ቁ.9? (ተጨማሪ ጥቅስ 2ቆሮ 5:17፣ኤፌ 2:10)
2. **መግቢያ ላይ በተጠቀሰው መሠረት የእግዚአብሔር መልክ እና ምሳሌ ማለት ምን ማለት ነው? በምንድ ነው የእርሱን መልክ መምሰል የምንችለው? (ቆላ 3:10 እና ኤፌ 4:24)**
3. ቆላ.3፡11 ከቁ.10 ጋር ምን ግንኙነት አለው?
4. ቆላ.3:11-12 በማንበብ የእግዚአብሔር ምርጦች የተባሉት ማንነታቸውን እና ልበሱ የተባለውን ዝርዝር ነገሮች ተወያዩ?
5. በቆላ.3:13 መሠረት አዲሱን ሰው ከለበሰን በኋላ በግንኙነቶቻችን መካከል በይቅርታ ህይወት መመላለስ አስፈላጊነቱ ምንድ ነው ለዚህስ ምሳሌያችን ተወያዩ?
6. በቆላ.3:13 ሐዋርያው ስለ ፍቅር ሲጽፍ የፍጻሜ ማሰሪያ እንደሆነ ይገልጻል። ምን ማለት ነው?
7. በቆላ 3:15-16 እነዚህን ልብሶች ለመልበስ አቅም እንዲሰጣቸው ወይም እንዲያገኙ አድርጉ ብሎ የሚያዛቸው ነገሮች ምንድ ናቸው?
8. ከዛሬ ጥናት የተማርነውን ካስረዳን በኋላ የሚጎድለንን ልብሶች እያሰብን እንጸልያለን።

***መደምደሚያ***

በመግቢያችን ላይ እንዳልነው ክርስትና የአዕምሮ እውቀት ብቻ ወይንም ጽንሰ-ሐሳብ (theory) ብቻ አይደለም። ክርስትና በተግባርና በአኗኗር የሚተገብር እውነት ነው። ክርስቶስ ብቃታችን ነው፣ በክርስቶስ ድነት አግኝተናል፣ ከክርስቶስ ጋር ሞተን ተነስተናል ስንል፣ ነገሩ በወሬ ብቻ ሳይሆን በተግባርም፣ በሕይወት ልምምዳችንም ይህ እውነት ሊታይ ይገባዋል። በዚህም መሰረት ሐዋርያው ጳውሎስ ከክርስቶስ ጋር ሞተን እንደተነሳን አማኞች፣ አሮጌን ማንነት ገድለን አዲሱን ሰው በአዲስና ሰማያዊ በሆነ አኗኗር እንዲንኖር ያሳስበናል።

**ጥናት አስራ ሁለት**

**የተለወጠ አማኝ የአኗኗር ሥርዓት**

**የንባብ ክፍል ፡- ቆላ 3:18-4:6**

**"23 የምታደርጉትን ሁሉ ለሰው ሳይሆን <u>ለጌታ እንደምታደርጉት</u> ቈጥራችሁ በሙሉ ልባችሁ አድርጉት፤** 24 ከጌታ ዘንድ እንደ ብድራት የምትቀበሉት ርስት እንዳለ ታውቃላችሁና፤ **<u>የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስን</u>** ነው" **(ቆላ 3:23-24)።**

**ዓላማ**

አዲሱን ሰው የለበሰ አማኝ በቤተሰብ ውስጥና ከቤት ውጪ እንዲሁም በአገልግሎቱ የሚኖረው ግንኙነት ከአዲሱ ማንነቱ ጋር አብሮ የሚሄድና አድራጎቱ ሁሉ ለጌታ እንደሚገባ መሆን እንዳለበት ማሳሰብ!

**መግቢያ፡**

**ሐዋርያው ጳውሎስ አሁን የአማኝ ግንኙነትን እያጠበበ አመጣው። ማለትም ግንኙነትን ወደ ቤተሰብ፣ወደ ሥራ እና ሌሎችንም ግንኙነቶች ጋር ይሄዳል። የዚህ ሁሉ መሪህ ለጌታ ብለን ማድረግ ነው (ቆላ 3:23-24)።** ባለፈው ጥናታችን በጌታ የዳነ ሰው አሮጌውን ማንነቱን እንዳረጀና ሊጣል እንደሚገባ ልብስ አውልቆ ሊጥለውና በጌታ ያገኘውን አዲስ ማንነት እንደ አዲስ ልብስ ሊለብሰው እንደሚገባ ተመልክተናል። ግን ይህ አዲስ ማንነት በግንኙነት ውስጥ ምን ይመስላል? ብለን ብንጠይቅ የዛሬው ጥናታችን መልስ ይሰጠናል። ግንኙነት ስንል ክርስቲያን እንደ ባል፣ እንደ ሚስት እንደ ልጅ እንደ ሰሪና አሰሪ እንዲሁም በውጪ በጌታ ባልሆኑ ዘንድ ያለውን ግንኙነት ይጨምራል።

እንግዲህ በዛሬው ጥናታችን ባጭሩ አንድ አማኝ አዲሱን ሰው ለብሶ በቤት ውስጥ በውጭ እንዲሁም በአገልግሎት በሚኖረው ግንኙነት ውስጥ ሊኖረው የሚገባውን አካሄድ ያሳየናል። ለምን እንገዛ? ለቆላስይስ የመከረውን ምክር ለኤፌሶን አማኞች ይመክራል **"ለክርስቶስ ካላችሁ አክብሮታዊ ፍርሀት የተነሣ አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተገዙ" (ኤፌ. 5:21)።**

**ትንታኔ (ማብራሪያ)**

ከላይ በመግቢያው እንደጠቀስነው **ቆላ.3:18-4:6** ባለው ሐዋርያው ጳውሎስ አማኝ አዲሱን ሰው እንደለበሰ ክርስቲያን በግል በቤት (በቤተሰብ) ውስጥ ሊኖረው ስለሚገባ አመላለስና በውጪ በማያምኑ ሰወች ዘንድ ሊመላለስበት የሚገባውን ሕይወት ያስገነዝባል።

**በቁ.18** ላይ ለሚስቶች ማሳሰቢያ ይሰጣል። “ሚስቶች ሆይ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ” ሲል ያዛል። እዚህ ጋ ሁለት ነጥቦች ልብ ሊባሉ ይገባል። በመጀመሪያ ሚስቶች ለባሎቻቸው መገዛት ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም “ተገዙ” የሚለው ቃል በአማርኛችንም ሆነ በእግሊዝኛ እምብዛም ግልጽ ባይሆንም፣ አሳቡ **ሚስቶች በፈቃዳቸው፣ ፈልገውና አምነውበት ራሳቸውን እንዲያስገዙ የሚያሳስብ** ነው። ይህ ሲባል ጌታ ኢየሱስ ምንም በመለኮትነቱ ከአብ እኩል ቢሆንም በፈቃዱ ራሱን ለእግዚአብሔር አስገዝቷል። ሚስቶችም እንዲሁ በሰውነታቸውና በፍጥረታቸው ከባል ወይንም ከወንድ ባያንሱም፣ ግን በአንድ ቤት ሁለት መሪ ስለማይኖረ፣ በፈቃዳቸው ራሳቸውን እንዲያስገዙ ያሳስባል። በሁለተኛ ደረጃ፣ ይህ የሚስቶች ለባል መገዛት **በጌታ የሚገባ ነው**። ወይንም ጌታን ደስ የሚያሰኘውና ተገቢ የሆነ አመላለስ ነው። ስለዚህም በቤት ውስጥ ሚስት ከባል ጋር መፎካከር፣ እና “እሱ ማን ስለሆነ ያዛል” በሚል መንፈስ ሳይሆን ጌታን ደስ ይሚያሰኘው ይህ ነው በሚል እንዲገዙ ይገባል። እባካችሁ ለዚህ አሁንም ኤፌ 5:21ን አንብቡት።

በቁ 19 ለባሎች ትዕዛዝ ሲሰጥ “ባሎች ሆይ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው” ይላል። እዚህ ጋር ልብ ሊባል የሚገባው፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ሚስቶችን ተገዙ እንዳለው ባሎችን ደግሞ **ግዙ አይልም ይልቅስ ውደዱ** ነው የሚለው። ምንም እንኳ ቤትን መምራትና መግዛት የባል ድርሻ ቢሆንም፣ ግን ሐዋርያው ጳውሎስ ሊያሳስብ የፈለገው ይህንን ድርሻ ባል የሚወጣው

በአምባገነንነት ሳይሆን በፍቅርና በመተሳሰብ እንደሆነ ያስገነዝባል። ይህ ኃላፊነት በፍቅር ስራ ላይ ሊውል እንደሚገባ እንደገና ለማሳሰብ “መራራም አትሁኑባቸው” ይላል። ስለዚህም ባል ትልቁ ሃላፊነቱ ሚስቱን በፍቅርና በመተሳሰብ እንዲመራት ነው። ከዚህ ውጪ ግን በግድ፣ በቁጣና በአምባገነንነት መምራት በጌታ የሚገባ አይደለም።

በቁ 20 እና 21 የልጆችና የወላጆች ግንኙነት እንዴ ሊሆን እንደሚገባው ያስገነዝባል። ልጆች የተሰጣቸው ሃላፊነት መታዘዝ ነው። እዚህ ጋር ግን በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ ሲባል “ሁሉ” የሚለው ቃል **እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እስከሆነ ድረስ** መሆኑ መዘንጋት የለበትም። በሌላ በኩል ልጆች ለወላጆች መታዘዝ ያላባቸው **ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ስለሆነ** ነው። ሆኖም ሃላፊነት የተሰጠው ለልጅ ብቻ ሳይሆን ለወላጅም ነው። በእርግጥ እዚህ ላይ የሚጠቅሰው አባቶችን ነው ሆኖም ግን ወላጆችን የሚል አሳብ ሊይዝ ይችላል። ለምሳሌ እዚህ ጋ አባት ተብሎ የተተረገመው ቃል በዕብ 11:23 ላይ ወላጆች ተብሎ ተተርጉሟል። ስለዚህ እዚህ ጋ የተጠቀሰው ሃላፊነት እንዲያው የአባት ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ የወላጆች ሃላፊነት ይመስላል። ወላጆች ልጆቻቸውን ተስፋ እንዳያስቆርጧቸውና እንዳያስመርሯቸው ሊጠነቀቁ ይገባል። ይህንን መመረርና ብሎም ተስፋ መቁረጥ እንዲሁም የልብ መዛል ምን ሊያመጣ ይችላል ተብሎ ቢጠየቅ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ እዚህ ጋ መልስ አይሰጥም ሆኖም ግን ልጅን ልጅ ነው ብሎ የማይገባ፣ ልብን የሚሰብር ቃላት መናገር፣ በቅጣት ስም አላግባብ መደብደብ የመሳሰሉት ተገቢ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። ነገር ሁሉ በትልቅ ትዕግስት ማለትም መንፈሳዊ ልብስ በመልበስ መሆን አለበት።

ከ3:22-4:1 ድረስ በባሪያዎችና በጌቶች ዘንድ ሊኖረው ስለሚገባው አመላለስ ወይም አካሄድ ያሳስባል። ባሪያዎች የተሰጣቸው ትዕዛዝ በሁሉ ለጌቶቻቸው እንዲታዘዙና በትጋት እንዲያደርጉት ነው። **ይህንን ሲያደርጉ በሥጋ ለሚገዟቸው ጌቶቻቸው እንደሚታዘዙ ሳይሆን ለጌታ እንደሚታዘዙ አድርገው እንዲታዘዙ ያሳስባል**። ለዚህም ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል። **አንደኛ** ከጌታ ዘንድ

ብድራትን ይቀበላሉ። **ሁለተኛ** ምንም እንኳ የሚሰሩት በሰዎች ስር ቢሆንም የእውነት ግን የሚያገለግሉት ጌታን ነው። በእርግጥም ጌታን ስለሆነ የሚያገለግሉት ከጌታ አንድ ቀን ብድራትን ይቀበላሉ። ባይሆን ኖሮ ብድራታቸው በምድር ብቻ በቀረ ነበር። በሌላ በኩል የሚያገለግሉት ጌታን ስለሆነ ስራውን እንደማይገባ የማይወጣና ስራ የሚበድል ባርያ እንዲሁ የበደሉን ዋጋ ይቀበላል። በእግዚአብሔር ዘንድ አድልዎ የለም። ባሪያ ስለሆነ ወይንም በጌታ ስላለ የሚያለምጥ ባርያ ወይንም ስራተኛ ዋጋውን ከመቀበል አያመልጥም። በዚህ አገር አውድ በየትኛውም የበላይ እና የበታች የሥራ ኃላፊነቶችን ያመለክታል።

ግን ሃላፊነት የተሰጠው ለባሪያ ብቻ ሳይሆን ለጌቶችም ነው። ጌቶችም እንዲሁ ባርያን እንደ እቃ ሊያስተዳድሯቸው ሳይሆን በጽድቅና በቅንነት እዲያስተድድሩዋቸው ታዘዋል። ሁሉም ስለ ጌታ ብለው መሆን አለበት።

እንግዲህ በግል ሕይወት በቤተሰብ ውስጥ እንዴት ሊመላለሱ እንደሚገባቸው ካሳሰበ በኋላ ከዚህ ውጭ በግል፣ ከራሳቸውና በውጭ ካሉት ጋር እንዴት ሊኖሩ እንደሚገባ ከቁ 2-6 ባለው ያሳስባል። በመጀመሪያ ከቁ 2-4 ባለው በጸሎት የነቁ ሊሆኑ እንደሚገባ ያሳስባል። በዚያውም እግረመንገዱም ሐዋርያው ጳውሎስ ለራሱም አገልግሎት እንዲጸልዩለት ያሳስባል። ቀጥሎም በቁ 5 እና 6 ላይ በውጭ ባሉት ዘንድ በጥበብ እንዲመላለሱ ያዛል። አንደኛው መንገድ ደግሞ አንደበትን መግዛት እንደሆነ ያሳስባል።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. **በቆላ.3፡18** ላይ ለሚስቶች የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? ከፍሉስ ሚስቶች ከባሎች ልዩነት እንዳላቸው የሚያስተምር ነገር አለ? **ኤፌ 5:21** ይነበብ።
2. በቆላ.319 ለባሎች የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? የሚከተለውን ቃል በማንበብ አነጻጽሩ (ኤፌ 5፡25-32)
3. ቆላ.3:20 ለልጆች እና ለወላጆች የተሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? ወላጆች እንዳያስመርሯቸው ስል ምን ማለቱ ነው (ኤፌ 6:1)?

4. ቆላ.3፡22-25 በባሪያዎች እና በጌቶች መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት የሚነግረን ምንድን ነው? በአሁን ዘመን ባሪያ እና ጌታ እነማን ናቸው?
5. ቆላ.3፡18-25 "ለጌታ እንደሚገባ..."፣ "ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና..."፣ **"ጌታን እየፈራችሁ..."፣** "ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና"፣ "በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ታውቃላችሁና" የሚሉት ሐረጎች **የሚያስተምሩን ምንድን ነው?**
6. ቆላ.4፡2-6 በማንበብ የተረዳችሁትን ነገር አካፍሉ? ከላይኛው ሀሳብ ጋር ምን ግኑኙነት አለው?
7. ከዛሬ ጥናት ለለበስነው አዲሱን ሰው ስለሚመጥን ህይወት እና ባህርይ ምን ተማራችሁ?

**መደምደሚያ**

እንግዲህ በጥቅሉ ብናስቀምጠው አማኝ አዲሱን ሰው ለብሶ በሰማያዊ አስተሳሰብና ልኬት የሚኖር በመሆኑ በቤተሰብ ማለትም በባልና በሚስት፤ ከልጆች ጋር፤ ከጌቶችና ከባሪያዎች (ከአሰሪና ከሰራተኞች) ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ስራዓተ አኗኗር እግዚአብሄርን የሚያስከብርና የእርስ በርስ ኑሮን የሚያጣፍጥ መሆን ይኖርበታል። ይህንን የምናደርገው በጭንቅ ሳይሆን በተለወጠ ማንነት ስለ ጌታ ብለን ሥጋችንን አሸንፈን ነው።

# ጥናት አሥራ ሶስት
# ምሥጋና ሰላምታና ማጠቃለያ
# የንባብ ክፍል፦ ቆላ 4:7-18

**ዓላማ**

አገልጋዮች በህይወታቸው እና በአገልግሎታቸው መልካም ተግባራቸውንና ምሳሌነታቸውን በማሳየት እኛም እንደ አገልጋይ ሊኖረን የሚገባውን ባሕሪይ ለመጠቆም

**መግቢያ**

በስተመጨረሻም ከቁ 7 እስከ 18 ሐዋርያው ስንብቱን ያቀርባል። በዚህም ከእርሱ ዘንድ ወደ ቆላስይስ የሚመጡትን ወገኖች ያሳውቃል (ቁ 7-9)። በመቀጠልም ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን መልዕት በሚጽፍበት ጊዜ አብረውት ያሉትን እየጠቀሰ ሰላምታ ማቅረባቸውን ይዘግባል (10-14)። በመጨረሻም የራሱን ሰላምታና የስንብት ማስታወሻዎቹን ያሰፍራል (15-18)።

**ትንታኔ (ማብራሪያ)**

ይህንን የስንብት ክፍል ለየት የሚያደርገው ነገር መኖሩ ግን ግልጽ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ሰላምታ ያቀረቡ ወደ ስምንት ሰዎችን ይጠቅሳል። ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች በአገልጋይነታቸው የሚያስመሰግናቸውን መልካም ባህሪያቸውን ይጠቅሳል። ይህ በአንድ በኩል ሐዋርያው ጳውሎስ የአገልጋዮችን መልካም ጎን እንደሚያስተውል እንዲሁም መልካም ጎናቸውን በመጥቀስ ያበረታታቸው እንደነበር ሲያሳየን በሌላ በኩል የሚያስመሰግን መልካም የአገልጋይ ባህሪይ ምን እንደሆነ ያሳስበናል። ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሰዎች የተመሰከረላቸውን መልካም ምግባር ልብ ይበሉ።

ቲኪቆስ - የታመነ አገልጋይ፣ በጌታም አብሮኝ ባርያ የሆነ

አናሲሞስ - የታመነ እና የተወደደ ወንድም

አርስሮኮስ

ማርቆስ } በእግዚአብሔር መንግስት ከኔ ጋር የሚሰሩ እና ሐዋርያው ጳውሎስን ያጽናኑ

ኢያሱ

ኤጳፍራ - የክርስቶስ ባርያ፣ በጸሎት ይጋደላል፣ ስለወገኖች እጅግ ይቀናል

ሉቃስ - የተወደደው በሌላ አባባል ውድ እንደማለት ነው (ውድ እከሌ እንደሚባለው)

ዴማስ - ምንም አልተጠቀሰለትም ሆኖም ይህ መልዕክት በተጻፈበት ጊዜ በተጻፈው በፊልሞና መልዕክት ላይ ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር አብሮ የሚሰራ እንደሆነ ተጠቅሷል። ሆኖም ወደ ኋላ ላይ ግን ይህንን አለም ወዶ ከሐዋርያው ጳውሎስ መለየቱ ተጠቅሷል (1ኛ ጢሞ 4:10)።

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ሁሉ በመልካም ሲያነሳቸው፣ አገልግሎታቸውን እንደሚገባ እየተወጡ ያሉ ወገኖች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህም ዛሬ ራሳችንን እንድናይ የሚያደርገን ነገር ነው። አማኝ አዲሱን ሰው እንደለበሰ ክርስቲያን አካሄዱ ወይንም ስነ ምግባሩ መልካም እንዲሆን ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱም ትጋትን የተሞላ በሚያዩትም ዘንድ የሚመሰከርለት ሊሆን እንደሚገባ ያሳየናል።

ከዚህም የተነሳ ይመስላል በቆላስይስ ለነበረ አንደ አክሪጳ ለተባለ ወንድም አገልግሎቱን አጥብቆ እንዲይዝና እንዲወጣ ሐዋርያው ጳውሎስ “ከጌታ የተቀበልከውን አገልግሎት እንድትፈጽመው ተጠንቀቅ” በሉልኝ ሲል የሚያሳስበው። ይህ ሰው በአገልግሎት የተሰማራ መሆኑ በፊልሞና ቁ. 2 ላይ ተገልጿል። ሐዋርያው ጳውሎስ ግን የሚያሳስበው እስከፍጻሜው እንዲተጋበት ነው። ስለዚህም ይህ የስንበት ክፍል መልካም አገልጋይ ብቻ ሳይሆን እስከፍጻሜ የሚሄድ አገልጋይ መሆን ተገቢ እንደሆነ ያስገነዝባል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ቆላ.4:7 በማንበብ ስለ ቲኪቆስ ህይወት እና አገልግሎት ተወያዩ? ምን እንማራለን?
2. ቆላ.4:8 ባለው ክፍል የተጠቀሰው አናስሞስ ማን ነበር? (የፊልሞና መልዕክት)
3. ቆላ.4፡12-13 በማንበብ ስለ ኤጳፍራ ማንነት ተወያዩ? ስለ አገልግሎት ምን እንማራለን (ቆላ.1:7-8)?
4. ቆላ.4፡16ን ስናነብ ስለ ቅዱሳ መጽሐፍትን በተመለከት ከአሁኑ ዘመን ጋር በማነጻጸር እግዚአብሔርን የምናመሰግንበት ነገር ይኖረናል? ምን? የጌታ ቃል በእጃችን መኖሩ!
5. በቁ 17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለአግሪጳ የሰጠው ምክር እና ማሳሰቢያ ምንድ ነው ተነጋገሩ። ከእርሱ ህይወት ስለ ራሳችን ምን እንማራለን?
6. በአጠቃላይ ከዛሬው ጥናት አገልጋይ መኖት ስለሚገባው ባህሪይ እና አገልግሎት ምን ተማርን?
7. ማሳሰቢያ፡- እስከአሁን ከቆላስይስ መልዕክት የተማራችሁትን ነገር በሌላ የጥናት ቀን ጊዜ በመውሰድ ክለሳ አድርጉ። የምስጋና፣የጸሎት እና የህብረት ጊዜም እንድታደርጉ በትህትና እናሳስባለን ።

**መደምደሚያ**

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህን ሰዎች ሁሉ በመልካም ሲያነሳቸው፣ አገልግሎታቸውን እንደሚገባ እየተወጡ ያሉ ወገኖች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህም ዛሬ ራሳችንን እንድናይ የሚያደርገን ነገር ነው። አማኝ አዲሱን ሰው እንደለበሰ ክርስቲያን አካሄዱ ወይንም ስነ ምግባሩ መልካም እንዲሆን ብቻ ሳይሆን አገልግሎቱም ትጋትን የተሞላ በሚያዩትም ዘንድ የሚመሰከርለት ሊሆን እንደሚገባ ያሳየናል። ክርስቶስ ከሁሉ የበላይ መሆኑን በኑሮችን እና በአገልግሎታችን ማሳየት አለብን።